# የሰባኪው ምሳሌ

## 2ኛ መጽሐፍ

በወንጌላዊ ደመወዝ አበበ

በ1998 ዓ.ም ታተመ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት ወይም
መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

Copyright© Demewez Abebe
August 2005
All rights reserved.

አሳታሚና አከፋፋይ:-
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ. ቁጥር 127
ስልክ 349 32 52 / 551 29 73
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢ-ሜይል:- SIMmedia@ethionet.et

**Printed by SIM Press**

# ማውጫ

## ክፍል አንድ
### እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ትዳር

- በዛሬዋ ጀምበር....................1
- በግ አራዱ በግ ለልጁ....................2
- የጎዳና ልጆች....................3
- ከራስ በላይ ራስ....................5
- አሽሙርና ትዳር....................6
- አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ....................7
- የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ....................8
- ጭድ የሌለው ጭቃ....................10
- የእርግዝና መከላከያ ዘዴ....................11


## ክፍል ሁለት
### እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ኅብረትና ፍቅር

- አንድ ብር ለአንድ ወገን....................12
- አምስቱ ካልሲዎች....................13
- ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራል....................14
- ፍቅር እውር ነው....................15
- ከእኔ በላይ ለአሳር....................16


## ክፍል ሦስት
### እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን

- ወንደላጤውና ድመቷ....................17
- ሠላሳ ሁለት ጥርስ....................18


## ክፍል አራት
### ለእግዚአብሔር ስለ መኖር

- የጋለሞታ ልብስ....................19
- አልማዝ ባለጭራ....................20
- ሴትን ከጃለሁ....................21


## ክፍል አምስት
### ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት

- ሰይጣንን በቆመጥ....................22
- መስተፋቅር በሎሚ....................23
- አጋንንቱና ሥራ አስኪያጁ....................24
- ጥቁር አባቡሌ....................25
- ፈታኙን እምቢ በል....................27
- ኑር ያልኩት ይኖራል....................29
- በሕግ አምላክ....................30
- የመቃብር አፈር....................31
- ድንግል ማርያም....................33

## ክፍል ስድስት

### እግዚአብሔርን የሚስደስት ሕይወትና አገልግሎት


- ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ......34
- ገንፎ በቂቤ......36
- ጴንጤው በክሰኛ......37
- ሰላቢ የሰለበው ሀብት......38
- እግዚአብሔር አይዘበትበትም......39
- ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም......40
- የምድር ጨው ወይስ የእንግሊዝ ጨው......41
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ......43
- የአርባ ቀን ዕድሌ......44
- ደምህን አቁሜአለሁ......45
- ስኬት......47
- መገለጥ ወይስ ማጋለጥ......48
- ነብር በቤታችን አለ......50
- መንፈስ ቅዱስ የለም......51


## ክፍል ሰባት

### እግዚአብሔርን ስለ መጠበቅ


- በክሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል......53
- የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታል......55
- ጠብቀነው ጠብቀነው......56
- እግዚአብሔር ጊዜ አለው......57
- ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም......58


## ክፍል ስምንት

### እግዚአብሔርን በሙሉ ኃይል ስለ ማገልገል


- የአሜሪካን ፕሬዚዳንት......60
- የቂሣርን ለቂሣር......61
- ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሣ......62


## ክፍል ዘጠኝ

### እግዚአብሔርን አምኖ ከሞት ስለ መዳን


- ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ......63
- የአስቂዋ ልጆች......64
- ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት......65
- የተበላ እቁብ......66
- ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም......67
- ጊወርጊስ ወይስ ዮሐንስ......68
- የፋሲካው በግ......69
- ይሉኝታ ይገድላል......70

## ክፍል አሥር

### ለእግዚአብሔር ስለ መስጠትና መስጠት


- ኮርሸምሸምሸምሸምሸም ........ 72
- ኢንቨስተሩ ........ 73
- የፈረንጅ ላም ........ 75
- ዲቪ ቢወጣልኝ ........ 76
- ኑሮ ጨምሯል ........ 77
- እንደ አንበጣዎች ነን ........ 78
- ችግሬ ክሶኝ ተከሰከሰ ........ 80
- እናቴ ጆሮዬን በላችው ........ 82
- መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም ........ 84


## ክፍል አሥራ አንድ

### ስለ እግዚአብሔር ቃል


- የጨረቃ ቤት ........ 85
- የሌባ ዓይነ ደረቅ ........ 86
- እኔም ዜሮ ነኝ ........ 87
- ኢየሱስ ሳሎን ቤት ነው ያለው ........ 88
- በኤፌሶን ይገፎታለሁ ........ 89
- በውሻ የተበላው ስብከት ........ 90
- ለካስ ለበጎ ነው ........ 92
- ሚስቴ ሞገሴ ናት ........ 94
- መሐይሙ እሥረኛ ........ 95


## ክፍል አሥራ ሁለት

### ግብዝነት ስለሌለበት እውነት


- ገመድ ሰርቄአለሁ ........ 97
- በወገቡ የተጠመጠመው እባብ ........ 98
- ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል ........ 99
- ጾም ጸሎት ........ 101

# ማስታወሻ

ይህንን መጽሐፍ በአገልግሎቴ ሁሉ ከጎኔ በመቆም አብራኝ ለተሰለፈችው፣ ለምትጸልይልኝ፣ ለምትመክረኝ፣ እና ለምታበረታታኝ ለምወዳት ለውዷ ባለቤቴ ለወ/ሮ የሺወርቅ ሽመልስ፣ እንዲሁም በጣም ለምወዳቸው ልጆቼ ለቤተልሔም ደመወዝና ለሃሌሉያ  ደመወዝ እንዲሆን አበረክታለሁ።

# ምስጋና

ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ጤንነትን፣ ሰላምንና ጸጋን ያበዛልኝን አምላኬን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቤ አመሰግናለሁ:: በመቀጠልም፣ ከጎኔ ቆመው ያበረታቱኝን፣ የጸለዩልኝን፣ የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብ ከስሕተት ያረሙኝን፣ በመደጋገም የጻፉልኝን ሰዎች ሁሉ ለማመስገን እወዳለሁ:: እንዲህም ሆኖ ሳለ፣ በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ፈጽሞ ስሕተት የለም ማለት አይቻልም:: ሆኖም፣ የተፈጠረ ስሕተት ቢገኝ በተገኘው ስሕተት ተወቃሹ እኔው እራሴው እንጂ እነዚህ ሰዎች አይደሉም:: የአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን፣ ወንጌላዊያንና ምእመናንን ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ:: እንዲሁም ባለቤቴን ወ/ሮ የሺወርቅ ሽመልስን፤ ወ/ም ዳንኤል ኃይሉን፣ ወ/ም ናይእግዚ ጎሩይን፣ ወ/ም ዘነበ ገ/ሐናን፣ እኅት አለምፀሐይ እውነቱን፣ እና እኅት የሺመቤት ደምሴን እግዚአብሔር አምላክ ያክብርልኝ፣ ሰላም፣ እድሜና ጤና ይስጥልኝ እላለሁ::

# መግቢያ

የሰውን አእምሮና ልብ በራሱ ፈቃድ እንዲከፍት አድርጎ በአእምሮው ውስጥና በልቡ ተቀምጦ ሳይረሳ ሁልጊዜ የሚኖር ቢኖር በምሳሌ የተላለፈ ትምህርት ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በሥጋ በተመላለሰበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ሕዝቡን በማስተማር ነበር። ታዲያ ትምህርቱ የሚያርፈው መሬት ሳይሆን የሰው ልብ ላይ ነበር። እርሱ በሚያስተምርበት ጉባኤ ያለ ሰው ሁሉ ለአፍታም አሳቡ ተሰርቆ ወይም ተሰላችቶ እንደ ነበረ አንድም ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ አናነብም። የዚህ ምሥጢሩ ምን ነበር? አንዱ ምሥጢር ተገቢና ልብን አንጠልጣይ ምሳሌ መጠቀሙ ነው።

የዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት አካባቢ ከሰማኋቸው ብዙ መልእክቶችና ትምህርቶች ውስጥ አብዛኛዎቹን አላስታውስም፣ ጥቂቶቹን ግን አስታውሳለሁ፤ ምክንያቱም በብዙ ምሳሌ ወደ ውስጤ ገብተው ነበርና ነው። እንዲሁ ዛሬም በሰዎች ልብ ውስጥ ቀርተው ፍሬ ሊያፈሩ የቻሉ ትምህርቶችን ስናጠና የምሳሌን ኃያልነት ሳንጠቅስ አናልፍም።

እኔም ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ዋናው ቁም ነገር ይህ ነው። ሕይወት ሰጪ የሆነውን ወንጌል ስናስተምር ከትምህርቱ ጋር በትክክል የሚሄዱ ምሳሌዎችን ብንጠቀም በሰዎች ልብ ውስጥ ሠርፆ መቅረቱ አሌ የማይባል ሐቅ ነው። ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ መጋቢዎች፣ ቄሶች፣ የወንጌል አስተማሪዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች፣ እንዲሁም ወንጌልን ለሌሎች ለማስተማር የሚፈልጉ ሁሉ እንዲጠቀሙበት እመክራለሁ።

በመጨረሻም፣ ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ በተለያየ መንገድ ከጐኔ ተሰልፈው የረዱኝንና ያበረታቱኝን፣ እንዲሁም ከውድ ጊዜያቸው ላይ ቆርሰው ጽሑፉን አንብበው በማረም ያገዙኝንና ጠቃሚ ምክር እና አስተያየት የሰጡኝን ሁሉ አመሰግናለሁ። ይህንን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሰዎች ሁሉ ጠቃሚና ሕይወት ለዋጭ የሆነ ትምህርትና አሳብ እንዲያገኙበት ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

ወ/ሮ ደመወዝ አበበ

# እርስዎም ይሞክሩት!

አብዛኛዎቹ በዚህ መጽሐፍም ሆነ በአንደኛው መጽሐፍ ላይ የሰፈሩት ምሳሌዎች ከእውነተኛ የሕይወት ታሪክ የተወሰዱና በሀገራችን ኢትዮጵያ የተፈጸሙ ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ላይ ያሉት ምሳሌዎች ሁሉ የሀገር ሀብት ናቸው ማለት ነው።

ዛሬም ሁለተኛውን መጽሐፍ ይዤ ወደ ውድ አንባቢያን ብቅ ስል፣ ለቀጣዮቹ ተከታታይ መጻሕፍት የአንባቢያንን ገንቢ አስተያየትና ተሳትፎ በሰፊው እየጋበዝኩ ነው።ከዚህም በኋላ የሰባኪው ምሳሌ መጽሐፍ የሕዝቡን የኅብረት ሥራ ያካተተ፣ ከሕዝቡ ወጥቶ ለሕዝቡ የሚጠቅም እንዲሆን አስቤአለሁ። ስለሆነም ቀጣዩን መመዘኛዎች በማሟላት ፈቃደኛ የሆነ ሁሉ ምሳሌዎችን በአድራሻዬ ቢልክልኝ ለመጽሐፍ እንዲሆን አቀነባብሬና አስተካክዬ ምሳሌውን ከላኪው ሙሉ ስም ጋር የማሳትም መሆኔን በደስታ ለአንባቢያን እገልጻለሁ። ሆኖም፣ ምሳሌው በመጽሐፍ ላይ ታትሞ የሚወጣው የሚከተሉትን መመዘኛዎች አሟልቶና ሚዛን ደፍቶ ሲገኝ ነው፦

1. እውነተኛ ታሪክ ከሆነ፣
2. ምንጩ የተጠቀሰ ከሆነ፣
3. ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ከሆነ፣
4. የላኪው ስም ከነአባት የሰፈረበት ከሆነ፣ እና
5. ሊነበብ በሚችል ጥሩ የእጅ ጽሑፍ የተጻፈ ከሆነ በቀጣዩ አድራሻዬ ላኩልኝ አስተናግዳለሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

ለወንጌላዊ ደመወዝ አበበ<br>
/ለእርስዎም ይሞክሩት ፕሮግራም/<br>
የመ.ሳ.ቁ. 70893<br>
አዲስ አበባ<br>
ኢትዮጵያ

# በግ አራጁ በግ ለልጁ

በዓመት ሁለት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታዘጋጀው የጋብቻ ትምህርት ለተሰበሰበው ምእመን የዕለቱ አስተማሪ እንዲህ እያሉ አስተማሩ:: '«ዛሬ እግዚአብሔር የሰጠንን ትዳር ዘወር ብለን 'እንደ እግዚአብሔር ቃል እየመራሁ ነው ወይ? የሚጠበቅብኝንስ በትክክል እየተወጣሁ ነው ወይ?' ብለን እንድናስብ እፈልጋለሁ:: በተለይም ለቤተሰቦቻችን በቂ ጊዜ የማንሰጥ አገልጋዮችም ጭምር። አንዳንዶቻችን ምናልባት ጠዋት ሰው ሳይነሣ ወጥተን ማታ ሰው ከተኛ በኋላ እንደ አልቤርጉ ለመተኛት ብቻ ይሆናል የምንገባው። ይህ ትክክል አይደለምና መስተካከል አለበት። ልጆች የአባትና የእናት ፍቅርን ማግኘት አለባቸው፤ ባልና ሚስትም እንደዚሁ። ዛሬ ብዙ ትዳር የሚበተነው ሀብት ከማጣት ብቻ ሳይሆን፣ ጊዜም ከማጣት ሆኗልና ክርስቲያኖች ሁሉ ለቤተሰባችን ከሁሉ አገልግሎት በፊት ቅድሚያ እንስጥ። ቤተሰብ ከአገልግሎት ይበልጣልና::» ለዚህም እጅግ በጣም አስፈላጊና ግሩም የሆነ መልእክታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«እንዳይርባቸውና እንዳይጠማቸው እንጂ ቤተሰቡ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው፣ ልጆቹ ከእርሱ የአባትነት ፍቅር እንደሚጠብቁ ያላወቀ አንድ በየክፍለ አገሩ እየዞረ የሚሠራ ሾፌር ነበር። ስድስትና ሰባት ወር ቆይቶ ሲመጣ ጤፍ፣ ከሰል፣ በግ ይዞ ይመጣና ሰጥቶ ሳምንት እንኳን ሳይሰነብት ተመልሶ ይሄዳል። የዚህ ቤተሰብ አባላት ሥጋቸው ባይራብም መንፈሳቸው ግን የአባት ፍቅር ርቦታል፤ በተለይ ትንንሾቹ ልጆች በልባቸው ቂም ይዘው ኖሯል። እንደዚሁ አንድ ቀን አባት ከስድስት ወር የክፍለ አገር ቆይታው በኋላ ለፋሲካ በዓል የሚሆን ሙክት በግ ይዞ መጣና ከቤቱ በር ላይ ለትንሹ ልጅ ሰጥቶ፣ ሌላ ሥራ ታዝዞ በጣም ስለ ቸኩለ ተመልሶ መኪናውን ይዞ ክፍለ አገር እንደ ሄደ ለቤተሰቡ እንዲነግር መልእክቱን ይሰጥና ይመለሳል። በዚህ ጊዜ የፋሲካን በዓል ከአባቱ ጋር ባለማሳለፉ በጣም የተናደደው ልጅ በጉን ይዞ ወደ ግቢ ይገባና እናቱን ጠርቶ 'እማዬ በግ አራጁ በግ አምጥቶልሽ ሄደ' ብሎ ተናገረ።»

አዎ ወገኖቼ፣ የእኛስ ልጆችና የትዳር ጓደኞቻችን ምን እያሉ ይሆን? ሥራና አገልግሎት እግዚአብሔር ከሰጠን ቤተሰብ አይበልጥምና እንመለስ። የአገር፣ የመንግሥት እና የቤተ ክርስቲያን ምንጩ ቤተሰብ ነውና ለቤተሰባችን ቅድሚያ እንስጥ። ጉዳናውን ለሞሉት የጉዳና ተዳዳሪዎች አንዱ ምክንያት ይኼ ነው:: ማንኛውም ተቋም (ድርጅት) ከመጀመሩ በፊት ቤተሰብ ተጀምሮ ነበር። እግዚአብሔር ቅድሚያ የሰጠውን ቤተሰብ እኛ ከሁሉ የመጨረሻ እንዳናደርገው ጌታ ይርዳን። አሜን።

*የቃል ጥናት ጥቅስ፣ "«ወደ ቤትህ በቤተሰቦችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደማረህ አውራላቸው አለው።»* (*ማር. 5:19*)

ግጥምጥም:- ቅድሚያ ለሚገባው ቅድሚያውን ሰጥቼ
ምሬትን ላስወግድ ከቤተሰቦቼ::

*ኢያሱ 24:15*
*ኢሳ. 8:18*

# የጎዳና ልጆች

ለባኪው የጋብቻ ትምህርት ለመማር ለተሰበሰቡበት ሰዎች ሁሉ እንዲህ እያሉ ትምህርታቸውን ቀጠሉ:: «ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ነው:: ከጋብቻ በፊት ያለ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ሲሆን፣ ከጋብቻ በኋላ ግን ንጹሕና የተቀደሰ ነው:: ከጋብቻ በፊት ልጅ መውለድ እንደሌለብን እንደምናውቅ ሁሉ፣ ከጋብቻ በኋላም የምንወልዳቸውን ልጆች ወስነንና አራርቀን መውለድ እንዳለብን ማወቅ ይገባል:: ብዙ ልጆች ወልደን እንደሚገባ ባለማሳደግ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት፣ ለአገርም ሸክም የሆነ ሥራ መሥራት የለብንም:: መጽሐፍ ቅዱሳችንን በደንብ ብንመረምር የሚጋጨው ማሳደግ የማንችላቸውን ልጆች በአናት በአናቱ ወልዶ እንደሚገባ ካለማሳደጋችን ጋር እንጂ፣ የምንወልዳቸውን ልጆች ወስነንና አራርቀን እንውለድ ከሚለው ጋር አይደለም:: ዛሬ በአገራችን ያሉ የጎዳና ልጆችን ብንመለከት በአቅማችን ወስነንና አራርቀን ካለመውለዳችን፣ ኃላፊነታችንን እንደሚገባ ካለመወጣታችን የተነሣ ከየቤቶቻቸው ተፈናቅለው የተበተኑ እንደሆኑ እንረዳለን:: ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ ሕዝቧን አጠንክራ ማስተማርና ሁለቱንም ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት የጋብቻ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ፣ ከተጋቡም በኋላ የሚወልዷቸውን ልጆች ስለ መወሰንና አራርቆ ስለ መውለድ የሚቻልበትን መንገድ ከሕክምና ባለሙያዎች እንዲረዱ መምከር አለባት::» ይህንንም ትምህርታቸውን በቀጣዩ ምሳሌ አብራሩ::

«አሥራ ሁለት ልጆችን ከመውለዳቸው የተነሣ የተቸገሩና ሌሎች ልጆችንም ላለመጨመር ያሰቡ ሁለት ባልና ሚስት ለየብቻ መተኛት ልጅ ላለመውሰድ ዋና መፍትሔ ነው ብለው እርምጃ ወሰዱ:: አንድ ቀን አሥራ ሁለቱም ልጆች ሁለት ብርድ ልብስ እየተጋፈፉ ወለሉ ላይ ተኝተው ነበር:: በዚህ መካከል ትልቁ ልጅ ቁጭ ብሎ በብስጭት "ድራማውን" ያይ ነበር:: ብርድ ልብሱ ከአንድ ወገን ሲስቡት ከሌላ ወገን ባዶ ሲሆን፣ አንዱ ሲለብስ ሌላው ራቁቱን ሲሆን አየና ለምን ከገቢያቸው ጋር የተመጣጠኑ ልጆችን ቤተሰቦቹ እንዳልወለዱ በደረቁ ሌሊት ቁጭ ብሎ እየተበሳጨ አሰበ:: አባታቸውም ልጆቹ በተኙበት በኩል ዳር ዳሩን እግሩን በቀስታ እያነሣ ወደ ባለቤቱ መኝታ ቤት ሲያዘግም፣ ቁጭ ብሎ የሚጋፈፉትን ልጆች ድራማ ይከታተል የነበረው ትልቁ ልጅ አባቱን አየውና፣ "እኛ ብርድ ልብስና አንሶላ እዚህ

እንጋፈፋለን አንተ ሌላ ለመጨመር እያደባህ ትሄዳለህ፣ ተመለስ ብሎ መለሰው።»

አዎ፣ ማሳደግ የማንችለውን ልጅ መውለድ በእግዚአብሔርም በሰውም፣ በትውልድም ዘንድ ተወቃሽ ያደርገናልና እንጠንቀቅ። በቀረልንም ዘመን ወስነንና አራርቀን በመውለድ የእግዚአብሔርን ስጦታዎች እንደሚገባ ማሳደግ እንድንችል ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- «ምድሪቱን ሙሉ» ብሎ ጌታ ቢልም፣

ተባብረን ነው እንጂ ብቻህን አትሞላም።

> ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም። (ምሳሌ 22:6)

# ከራስ በላይ ራስ

ሰባኪው፣ "ባልና ሚስት እንድንከተለው የተሰጠን መመሪያ በቃሉ ውስጥ ነው፤ ቃሉም እግዚአብሔር የክርስቶስ፣ ክርስቶስም የባል፣ ባልም የሚስት ራስ ነው ብሎ ማንም ሊሽረው የማይችለውን ደረጃ አስቀምጧል። በዘመናችን ግን ይህንን ስንሽር እንገኛለን። አንዳንድ ቤት ራስ ባል መሆኑ ቀርቶ ሚስት ሆና ትገኛለች። ስለሆነም እግዚአብሔር በቃሉ ያስቀመጠው ቅደም ተከተል ተዛብቷልና ቤቱ ሲበላሽ፣ ፍቅርና ሰላም ሲጠፉ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ ባል ሚስቱን ይውደድ ሚስትም ለባሏ ትገዛ ነው የሚለው። ይህ መዛባት የለበትም። ሁሉም እንደ እግዚአብሔር ቃል ኃላፊነቱን እየተወጣ አንዱ ለሌላው በክርስቶስ ፍርሃት እየተገዛ ሲኖር ነውና የሚያምረው፣ ያለ ቦታችሁ የሌላ ሰው ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ሁሉ ወንበሩን ልቀቁ። ያን ጊዜ ሰላም፣ በረከትና ደስታ ወደ ቤቶቻችሁ ይመጣሉ" ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

መጋቢው በቤተ ክርስቲያናቸው ለጋብቻ ትምህርት ለተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ፣ «ጋብቻ የሚያምረው እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥርዓትና ደረጃ ሲሄድ ነው። የሚስት ራስ ባል ነውና፣ ራስ የሆናችሁ ሴቶች ዛሬ ሥራችሁን ቀይሩ» እያሉ ያስተምራሉ። በዚህ መካከልም አንድ የሚያስገርም ጥያቄ ተጠየቁ። «እስቲ ሴቶች የበላይ ሆነው የሚያስጨንቋችሁና የሚያዟችሁ፣ የቤቱን አስተዳደር ለሴቶች የለቀቃችሁ ሁሉ ተነሡ።» በዚህ ጊዜ በጉባኤው ውስጥ ያሉት ወንዶች በሙሉ ተነሡና አንድ ወንድ ብቻ ሳይነሣ ቀረ። መጋቢውም፣ «ጥሩ እንግዲህ አንድ ሰው ብቻ ነው ራስ ሆኖ ቤቱን በማስተዳደር ላይ ያለ። ሌሎቻችን በቤታችን ራስ ሴቶች ብቻ ናቸው ማለት ነው» ብለው ወደተቀመጠው ሰው ዘወር አሉና፣ "የእኔ ወንድም፣ አንተ ያልተነሣኸው የቤቱ ራስና አዛዥ እንደ ቃሉ አንተ ስለሆንክ ነው አይደል?" ቢሉት፣ "አይ፣ አይደለም። ሚስቴ እዚያ ጋ ሆና በምልክት እንዳትነሣ ብላኝ ነው" ብሎ መለሰ።

አዎ፣ ትዳር የሚያምረው እንደ ቃሉ ባል ራስ ሲሆን ነውና የባልን ራስነት ሚስቶች አትውሰዱ፤ ይልቁንም ኃላፊነቱን ወስዶ ባል እንዲመራ እርዳታ ልታደርጉለት ይገባል። ከባላችሁ የበለጠ ደመወዝና ትምህርት ስላላችሁ እንዲሁም አፈ-ጮሌ ስለሆናችሁ የባላችሁን ቦታ መውሰድ አትችሉም።

ግጥምጥም:- *ከራስ በላይ ራስ እንዳለ ተረድተህ*
*ትዳርህን ምራ እግዚአብሔርን ፈርተህ*

| |
|---|
| *ኤፌ. 5፡22*<br>*1ኛ ጴጥ. 3፡7* |

# አሽሙርና ትዳር

የጋብቻ አማካሪው ሁለቱን ወጣቶች ቁጭ አድርገው ለዘለቄታ ትዳራቸው የሚጠቅማቸውን ትምህርት እንዲህ እያሉ ያማክራሉ፡፡ «እናንተ ወጣቶች በትዳር ዓለም ስትኖሩ ሁለት ነገሮች እወቁ፡፡ አንዱ፣ የክትና የዘወትር ባሕርይ እንዳለ፣ የክቱ አሁን ያላችሁበት፣ የዘወትሩ ደግሞ በኋላ ስትጋቡ የሚወጣው ነው። ሌላው፣ ሁልጊዜም በግልጽነት ተነጋግራችሁ መጨረስ እንጂ በኩርፊያና በአሽሙር ንግግር እርስ በርስ እየተቆሳሰላችሁ መኖር እንደሌለባችሁ ነው፡፡» በተጨማሪም ይህንን ምሳሌ አከሉበት፡፡

«ሁለት በግልጽነትና በአሽሙር ንግግር ከአሥር ዓመት በላይ ቆይተው ልጆች ወልደው የተፋቱ ባልና ሚስት አውቃለሁ፡፡ ሁልጊዜ ሚስት ከባሏ ምን እንደምትፈልግና እንደሚፈለግባት አታውቅም፣ እርሱም እንደዚሁ። ልጆችም ከወለዱ በኋላ ጭቅጭቁ በልጆች ሁሉ ፊት ስለ ዘለቀ ልጆች 'ባልና ሚስት' የሚባለውን ቋንቋ መስማት ያስፈራቸው ጀመር። በትምህርት ቤት እንኳን ከጓደኞቻቸው ጋር የባልና ሚስት ድራማ ሲሠራ ይህንን ገጸ-ባሕርይ ተላብሰው መሥራት አይፈልጉም። የአባትና እናታቸው መጥፎ ምሳሌ በአእምሮአቸው ተቀርጾባቸዋልና ልጆቻቸውን እንኳን በመልካም አስተምረው ማሳደግ አልቻሉም። አስታውሳለሁ በመጨረሻ እንኳን ለመለያየት ምክንያት የሆነው የሚስቲቱ የአሽሙር ንግግር ነበር። ታሪኩ እንዲሁ ነው። ልጁ ት/ቤት ሲማር አንድ ያልገባውን ጥያቄ ቤተሰብ አለኝ ጥያቄዬን ይመልሱልኛል ብሎ ይዞ ይመጣል። እናቱንም 'እማዬ ዛሬ በት/ቤት የሰው ዘር የመጣው ከዝንጀሮ ነው የሚል ትምህርት ተማርኩ፣ እና እኔ የመጣሁት ከዝንጀር ነው ማለት ነው?' ብሎ ሲጠይቅ፣ እናት ቀናና ትክክለኛ የሆነውን ወይም ከዝንጀሮ አለመምጣቱን ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ በአምሳሉ ከአፈር እንደ ሠራው በመናገር ፈንታ ቀና ብላ በቁጣ፣ 'እኔ ምን አባክ አውቅልሃለሁ፣ አባትህ ዘሮቹን አላስተዋወቀኝም ብላው አረፈች፡፡»

አዎ፣ አብሮ መኖርን የመሰለ ከባድና ጥሩ ነገር የለም። ሁለት ባሕርይ በአንድ አስማምቶ ለማስኬድ የጌታ ጸጋ ያስፈልጋል። ግልጽነትና ቅንነት፣ ንጹሕ ልብና ገርነት ያስፈልጋል። ያን ጊዜ ቤት ሰላም ይሆናል፣ ሰላማዊ፣ በፍቅርና በእውነት የታነጸ ዜጋን መተካት ይቻላል። ስለዚህም የዘወትሩን የባልና የሚስት ባሕሪ ከእኛ ጋር ያለማቋረጥ ሆኖ በሚረዳንና በሚያስችለን ጌታ እንድናልፈው እርሱ ራሱ ያግዘን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- *«የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸው»* (ኤፌ. 5:4)፡፡

ግጥምጥም:- እግዚአብሔር የጠላውን ለምን ትወዳለህ፣
በሰላም የሚያኖር ክርስቶስ እያለህ።

*ኤፌ. 4:25-32፣5:2*
*ገላ. 6:2*

# አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ

*መጋቢው*፣ «በአደባባይ ሲዞር የነበረ ሰይጣን ዛሬ መልኩን ለውጦ በጓዳ ቤተሰብን እያፈረሰ ይገኛልና ተጠንቀቁ። ይኸውም ዋና ዓላማው የክርስቲያኖችን ጋብቻ ከቻለ ማፍረስ፣ ካልቻለም ጤና ማሳጣት ነው። ዛሬ ብዙ ባለትዳሮች እርስ በርስ ካለመስማማት የተነሣ በአንድ ቤት እየኖሩ ተለያይተዋል፣ ለስሙ ብቻ ባልና ሚስት ናቸው ግን ለየብቻ ይተኛሉ። ወገኖቼ፣ እናስተውል፣ ይህ የሰይጣን ሥራ ነው አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ። አይተኛም እግዚአብሔር አምላክ ያጣመረውን ዓለም፣ ሥጋና ሰይጣን ሊለየው አይገባም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል ባልም ሚስቱን ሚስትም ባሏን እንደገዛ ሥጋቸው አድርገው ይወድዱ ዘንድ ይገባል (ኤፌ. 5:28)። ሰይጣን ዘዴውን በመጠቀም አንዳችንን በሌላችን ላይ ያስነሣል፣ አሳቡን እንድንፈጽም ባሕሪውን ያለብሰናል፣ እንድንጣላ ያደርጋልና ንቁ፣ ነቅታችሁም ተቃወሙት» ለሚለው ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ በማስከተል ተናገሩ።

«አንድ ጊዜ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን እያመለኩ እያለ ድንገት በአንድ ወጣት ውስጥ ክፉ መንፈስ ነበረና ቤተ ክርስቲያንን ይበጠብጣል። በጐኑ ያሉትን መማታት፣ መጮህ፣ መዝለልና መወራጨት ሲያበዛ አጠገቡ ያሉትም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና ያልበሰሉ ነበሩና ሊጠጉት ፈሩ። በዚህ ጊዜ አንድ አማኝ ከሌላው ረድፍ ተነሥቶ እየተንደረደረ መጣና ግጥም አድርጎ ይዞ 'ፀጥ በል' አለው። በወጣቱ ውስጥ ያለውም አጋንንት 'እነዚህ ሰዎች ሁሉ ከአጠገቤ በርግገው ሸሽተው አንተ እንዴት ልትደፍረኝ ቻልክ?' ቢለው፣ ሰውዬው እየተበሳጨ፣ 'የአንተ ታናሽ እኅት እቤት ስላለችኝ ተለማምጀሃለሁ' ብሎት አረፈ። (ታናሽ እኅት የሚላት እንደ ሰይጣን ባሕሪ ተላብሳ ቁም ስቅሉን የምታሳየውን ባለቤቱን ነበር)።»

አንባቢ ሆይ፣ ቤትህ ገነት ነው ወይስ ገሃነም? ገነት ከመሰለና ሰላም ከሰፈነበት አመስግን፣ ነገር ግን ገሃነም ከመሰለ ወይ አንተ ወይ ሚስትህ ወይም ሁለታችሁም የሰይጣንን አሳብና የዓለምን ፈቃድ ተከትላችኋልና ተመለሱ። እግዚአብሔር ጋብቻን ሲጀምረው በመረዳዳትና በመግባባት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽም እንጂ ትእዛዙን በመጣስ እንደ ሔዋን መሣሪያ ለመሆን አይደለምና እንጠንቀቅ። እግዚአብሔር ትዳርን እንደሚፈልገው መምራት እንድንችል ጌታ የሥጋ ሥራንና የሰይጣንን አሳብ በኃይሉና በችሎታው ያስወግድልን። አሜን።

*የቃል ጥናት ጥቅስ*፦ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን» (ዕብ. 13:4)።

| |
|---|
| *መክ*. 9:9 |
| *ማቴ*. 13 |

*ግጥምጥም*:- ከራስ በላይ ራስ እንዳለ ተረድተን፣

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንኑር ተስማምተን።

# የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ

መምህሩ፣ ስለ ትዳር መፍረስ ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ:- «ዛሬ የብዙዎች ትዳር ፈርሶ ልጆች የተበተኑት ወይም ከአንድ ጣራ በታች ባልና ሚስት እንደ ደባል ተኮራርፈው የሚኖሩት ለምንድን ነው? ብንል የምንጋጭባቸውን ነገሮች ጠንቅቀን አውቀን መፍትሔ ባለመፈለጋችን ወይም አውቀን በግዴለሽነት በመተዋችን ነው:: ለመሆኑ ከእነዚህ ነገሮች ዋና ዋናዎቹ ምንድን ናቸው? ገንዘብ፣ ግንኙነት /Communication/፣ ዘመድ፣ ግብረ-ሥጋ፣ ልጆች፣ መንፈሳዊነት ናቸው:: የእግዚአብሔር ቃል እነዚህን ሁሉ በጋራና በኅብረት፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት እንድናከናውናቸው ያዘናል:: ያኔ የሁለቱ ተጋቢዎች ፍቅር ይጨምራል:: ለምሳሌ፣ ዘመድን ብንመለከት ብዙ ጊዜ ግጭት የሚያመጣው የባል ዘመዶች ቢሆኑ "የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ" የሚለው ከቃሉ ያፈነገጠ አባባል አስወግደን በጋራ መፍትሔ መፈለግ አለብን::

ለዚህ ትልቁ ተዋናይ ሚስት ናት፤ የእርሱ ዘመዶች የእኔም ናቸው በማለት ልቧን ብትከፍትና የሚደረገው እርዳታ ሁሉ በእርሷ በኩል ቢፈጸም ሰላም ይመጣል:: ባልና ሚስት የሁለታቸውንም ደመወዝ ማወቅ አለባቸው:: ጊዜ ሰጥተውም ወጪያቸውን ከገቢያቸው ጋር ማጣጣም ያስፈልጋቸዋል:: የእኔ የሚሉት ሃብት አይኖርም፤ በባንክም ገንዘብ ሲያስቀምጡ በጋራ ስም እንጂ በአንዱ ወገን ብቻ መሆን የለበትም:: ሌላው ግንኙነት ነው:: በጋብቻ ግልጽነት የተሞላበት ንግግር ያስፈልጋል እንጂ አሽሙር ወይም ደካማ ጐንን እያነሡ በነገር መውጋት ተገቢም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለምና እናርም:: ሌላው ግብረ ሥጋ ነው:: ባልና ሚስትን የሚያጋጨው ይህንን አስደሳች ነገር ለማድረግ አለመነጋገር፣ ባህል፣ ይሉኝታና መተፋፈር ናቸው:: እነዚህን ማስወገድና አለመከላከል ፍቱን መድኃኒት ነው:: ሌላው ልጆች ናቸው:: እነዚህን የእግዚአብሔር ስጦታ ተገቢ ጊዜ በመስጠት በጋራ ማሳደግ እንጂ ለአንዱ ወገን ብቻ የሚተዉ ዕዳዎች አይደሉም:: የመጨረሻው ባልና ሚስትን የሚያጋጨው ነገር መንፈሳዊነት ነው:: ባል ወይም ሚስት፣ "ድሮም ቢሆን ያለኸው (ያለሽው) በእኔ ጸሎት ብቻ ነው" ብሎ በመውቀስ መንፈሳዊነትን አጉልቶ ከማሳየት ይልቅ፣ በደከመበት ወይም በደከመችበት እያበረታቱ አብሮ ማደግ ያስፈልጋል::

እንግዲህ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ለትዳራችን ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል:: አለበለዚያ ሁሉንም አጥተነው እናድጋለን::» ስለዚህም ግሩም የሆነ ትምህርታቸው ማስረጃ እንዲሆን ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ብለው ተናገሩ::

«በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ የሚሠራ አንድ ሰው ነበረ:: ታዲያ ሁልጊዜ ቅድሚያ የሚሰጠው ለሥራው ነበርና ባለቤቱና ልጆቹ ከእርሱ ጋር የሚያሳልፉበት ጊዜ አጡ:: በሌሊት ይወጣል፣ በውድቅት ይገባል:: ባለቤቱም ስለዚህ ጉዳይ አናገረችው፣ አልሰማትም:: አስመከረችው፣ አላሻሻለም:: መጨረሻ ላይ ቢብስባት አንተ ያገባኸው እኔን ሳይሆን ሥራህን ነውና ደህና ሁን ብላ ጥላው ሄደች:: ሴቲቱ ወደ ቤቷ እንድትመለስ ቤተ ክርስቲያንም ብዙ ሞከረች፣ ግን አልቻለችም:: ሰውየውንም ጥሩ ምሳሌ አይደለምና ከሥራህ ልቀቅ ብላ አባረረችው:: ሥራውንም ትዳሩንም በአንድ ላይ አጣ::»

ወገኖቼ ሆይ፣ ቅድሚያ ለትዳራችን እንስጥ:: የውጭ ጠንካራ መሠረት ውስጡ ነው:: ውስጡ ፈርሶ ውጩን ብንገነባ እርካታ የለውምና ለትዳራችን የሚገባውን ጊዜ እንድንሰጥ ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- እስቲ ተረጋጋ መብከንከንህን ተው፣

ጊዜ አለመስጠት ነው ቤትን የሚያፈርሰው::

የቃል ጥናት ጥቅስ: «... ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ::» (1ኛ ጴጥ. 3:7)

| |
|---|
| ኤፌ. 5:33 |
| 1ኛ ቆሮ. 7:3-5 |

# ጭድ የሌለው ጭቃ

**የቃል ጥናት ጥቅስ: «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ በሽመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።» (ምሳ.22:6)**

ቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናቿ የጋብቻ ትምህርት እንዲማሩ ባዘጋጀችው ፕሮግራም ላይ ስለ ልጆች አስተዳደግ የሚያስተምረው መምህር እዚያ ለተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ እንዲህ እያለ ማስተማር ጀመረ። «በመጀመሪያ ደረጃ ጌታ ወደ እኔ ሲመጡ አትከልክሉአቸው ካላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ዋናዎቹ ልጆች ናቸው። ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙና የሰንበት ትምህርት እንዲማሩ ፍቀዱላቸው፣ አበረታቷቸውም። በእግዚአብሔር ቃል ተኮትኩተው ያደጉ ልጆች የቤተሰብ ተስፋዎች፣ የአገር ተረካቢዎችና የእግዚአብሔር ክብር መገለጫዎች ይሆናሉ። በተቃራኒው ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ተኮትኩተው ያላደጉ ልጆች የቤተሰብ መከራዎች፣ የሀገር ሸክሞችና የሰይጣን ክብር መገለጫዎች፣ በአጠቃላይም "ጭድ የሌለው ጭቃ" ይሆናሉና በንዳችሁ የምታሳድጉአቸውን ልጆች ለሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳቸውና ለአእምሮአቸውም ተጠንቀቁላቸው። ባልና ሚስት በአሳብ በምትጋጩ ጊዜ በልጆች ፊት አትጨቃጨቁ፣ ወደ መኝታ ቤታችሁ ግቡ እንጂ። በእግዚአብሔርና በልጆቻችሁ ፊት ቀናውንና የከበረውን አሳብ ሁልጊዜ ተነጋገሩ፣ እናንተ የልጆቻችሁ ምሳሌዎች ናችሁና። ደግሞም የልጆች አእምሮ ያልደረቀ ሲሚንቶ መሆኑን አውቃችሁ በመልካም ነገር ቅረጹአቸው፣ ሲያድጉ ከዚያ ፈቀቅ አይሉምና።» ለዚህ ግሩምና ፈዋሽ ለሆነ ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ አስከትለው ተናገሩ።

«አባትና እናት ትንሹ ልጃቸው መካከላቸው እንዳለ ረስተው ወይም እንደዚህ ያደርጋል ብለው ባለመገመት እቤታቸው እየመጡ ስለሚጎበኙአቸው ቄስ አበላል ይነጋገራሉ። "አይገርምም፣ እኚህ ቄስ ሲበሉ እኮ እንደ አሳማ ነው፣ የቀረበላቸውን ሁሉ አንድ ሳያስተርፉ ነው ጥርግ አድርገው የሚበሉት።" ይህንን ሲነጋገሩ የሰማና በአእምሮው የቀረጸው ልጅ አንድ ቀን ቄሱ በር ላይ ቆመው በር ሲያንኳኩ ሄዶ ከፈተላቸውና በሚከላተፈው አንደበቱ እንዲህ አላቸው። "እንደ አሳማ የሚበሉት ቄስ እርስዎ ነዎት?" ቄሱም በቆሙበት ድርቅ ብለው፣ "ማን ነገረህ ልጄ?" ሲሉት፣ "እማዬና አባዬ ሲያወሩ ሰምቼ ነው" አላቸውና አረፈው።»

ለመሆኑ፣ ልጆቻችንን እንዴት ነው እያሳደግን ያለነው? አእምሮአቸውን በመልካም ነገር እየገነባን ነው ወይስ መልካሙን ነገር ከአእምሮአቸው እያጋባን? ከክፉ ነገር እየመለስን ወይስ ሳናውቀው ክፉ ነገር እየከለስን? የልጆቻችን መጀመሪያ መጨረሻውን ይወስናልና ከመጀመሪያው እንድንጠነቀቅላቸው ጌታ ይርዳን። አሜን።

| | |
|---|---|
| **ግጥምጥም:- ልጅ በልጅነቱ ሲስተካከል ያምራል፣ ካደገ በኋላ ሲሰበር ይችላል።** | ምሳሌ 23:13<br>ምሳሌ 17:6 |

# የእርግዝና መከላከያ ዘዴ

ሰባኪው ስለ እርግዝና መከላከያ ዘዴ ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ:: «የዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከማውገዝ ይልቅ ማስተማርን ልማዷ ማድረግ አለባት:: ስለሆነም ዛሬ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ስለ ጋብቻ እና ልጆችን መጥኖ ስለ መውሰድ በግልጽ እንማራለን:: ጋብቻ በመተሳሰብና በመረዳዳት አብረን የምንኖርበት ተቋም ነው:: ጋብቻ ማለት የግልን ጥቅም በጋራ ጥቅም የምንለውጥበት የጋራ ስምምነት ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ትዳርን ስንመለከት ተቃራኒውን ነው የምናገኘው:: ለምሳሌ፣ እዚህ ላይ ልጆችን መጥኖ ስለ መውሰድ ሲነሣ ባሎች ፈቃደኛ አይሆኑም:: ልጅ ባናት ባናቱ ካልተወለደ ትዳሩ ትዳር አይመስላቸውም:: ይህ ደግሞ ወላጆችን በተለይም እናትና ልጆቹን ራሳቸውን ይጉዳል:: ስለዚህ ትዳር የፍቅርና የመተሳሰብ ተቋም ነው ካልን፣ ለሚስትም ማሰብ አለብን እንጂ ማኅጸኗን የተከራየን ይመስል በየዓመቱ ልጅን እንድትወልድ ማስገደድ የለብንም:: ደግሞ ለተወለደው ልጅ የሚገባውን አለማድረግ እኮ ኃጢአት ነውና እንጠንቀቅ:: የዚህ ዘመን ልጆች በድላቸው የሚያድጉ ብቻ ሳይሆን፣ በድሎትም የሚያድጉ መሆናቸውን አንርሳ:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮችና የሕክምና ባለሙያዎችን በማማከር የእርግዝና መከላከያ መጠቀም ጥበብ ነው እንጂ ኃጢአት አይደለም:: ይህ ሆኖ ባይገኝ የወለድናቸውን ልጆች ማሳደግ አቅቶን፣ "ለምን ወለድከኝ" የሚል የዘላለም ጠባሳና ወቀሳ በራሳችው በልጆቹ ይቀርባልና እንጠንቀቅ:: አገርን የሚያለሙ እንጂ አገርን የሚያወድሙ ልጆች አንውሰድ::» ለዚህም ግሩም ለሆነ ምክራቸው ማጠናከሪያ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አሥር ልጆች የወለዱ ባልና ሚስት ሌላ ተጨማሪ ልጆች እንዳይወልዱ ማቆም እንዳለባቸው ተመካከሩ:: ለጊዜውም የደረሱበት የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ለየብቻ መተኛት ሆነና ለየብቻ መተኛት ቀጠሉ:: ነገር ግን አንድ ቀን ባልየው ለብቻው ተኝቶ እስከ መቼም እንደማይዘልቀው በመረዳት ቃል ኪዳኑን ጥሶ ከአንደኛው ክፍል በሳሎን ቤት አቋርጦ ወደ መኝታ ቤታቸው ለመዝለቅ በዝግታ ድምፅ ተራመደ:: አሥሩም ልጆች የለበሷት ብርድ ልብስ አልበቃቸው ብላ ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ እየሳቡ ግማሹ ሲለብስ ግማሹ ባዶ ሲሆን ትልቁ ልጁ በንዴት ተበሳጭቶ ቁጭ ብሎ ይህንን ሁሉ ድራማ ይመለከት የነበር ይኸው ልጅ አባቱ ወደ እናቱ እንደሚሄድ አወቀና በከፍተኛ ድምጽ ጮኾ እንዲህ አለው:- «እኛ ብርድ ልብስ አንሶን እንገፋፋለን አንተ ሌላ ልትጨምር በደረቅ ሌሊት ታደባለህ፣ ተመለስ!» አለው::

አዎ፣ በእኛ አለማወቅና ንዝህላልነት ወይም የእርግዝና መከላከያን ዘዴ መጠቀም እንደ ኃጢአት በሚቆጥር ከቃሉ ጋር በማይሄድ አጉል መንፈሳዊነት ተሸብበን የትውልድ ተወቃሾች እንዳንሆን ልንጠነቀቅና እንደ እባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ ልንሆን ያስፈልገናል:: እንዲህ እንድንሆንም ጌታ ይርዳን:: አሜን::

**ግጥምጥም:-** ማሳደግ እምችለውን ወልጄ ብነሣ፣
እኔም እድናለሁ ከትውልድ ወቀሳ::

| |
|---|
| መዝ. 127፣3 |
| ኢሳ. 8:18 |

## *ክፍል 2*
## *እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ኅብረትና ፍቅር*

# አንድ ብር ለአንድ ወገን

ሰባኪው ስለ መስጠት እንዲህ ብለው አስተማሩ፡፡ «የመጨረሻው ጊዜ ደርሶ እኛ ወደ ጌታ ወይም ጌታ ወደ እኛ መጥቶ ወደ ዘላለሙ ቤታችን እስክንሰበሰብ ድረስ በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር እርስ በርሳችን ተዛዝነንና ተሳስበን ልንኖር ይገባል፡፡ ያለ ምንም ስስት ያለንን ለወገኖቻችን በማካፈል የእነርሱ ችግር ችግራችን ሊሆን ይገባል፡፡ መስጠት መንግሥት ሰማይ የሚያስገባ የደኅንነት ሥራ ባይሆንም፣ የዳነ ሰው ግን መስጠት ይጠበቅበታልና እንትጋ፡፡ ዛሬ ዓለም፣ "አንድ ብር ለአንድ ወገን" እያለች ሕዝብን ከረሃብ ለማትረፍ በምትሯሯጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው አብሮ በዘመቻው ሊሳተፍ ይገባል እንጂ በስስት ቆፈን ተይዘን እጃችንን አጣምረን ከዳር ቆመን ማየት አይገባንም፡፡ የእግዚአብሔር ሰው መቼም ቢሆን ከእኔ ይልቅ ለወንድሜ በሚል መልካም አሳብ መሽቀዳደም አለበት እንጂ፣ ሁልጊዜ የማይሞላውንና እንደ መሰላል የተያያዘውን ምኞቱን ብቻ እየተከተለ በመስጠት የሚገኘውን በረከት ሊያጣ አይገባውም፡፡ ሁልጊዜም ሁሉም ሰው ራሱን ሳያስቀድም ወንድሙን ቢያስቀድም ምድራችን የረሃብ ምድር ሳትሆን የበረከትና የፈውስ ምድር ትሆናለች፡፡» ለዚህም ግሩም ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ፡፡

«ሁለት ጓደኞሞች ምግብ ቤት ውስጥ ገብተው ምግብ አዝዘው ምሳቸውን እየበሉ ሳለ ሁለቱም በውስጣቸው አንድ ፈተና ውስጥ ገብተዋል፡፡ በቀረበላቸው ትሪ ላይ አንድ ትልቅና ትንሽም ዓሣ አብሮ ስላለ የትኛውን እንደሚወስዱ ሁለቱም ተቸግረዋል፡፡ በዚህ መካከል የትሪው እንጀራ አልቆ ዓሣዎቹ ብቻ ስለቀሩ እንደተመኘው አንደኛው ትልቁን ዓሣ ብድግ አድርጎ መብላት ሲጀምር፣ ሁለተኛው ተቆጥቶ እንዲህ ማለት ጀመረ፣ "አንተን ሁልጊዜ ታዝቤሃለሁ፡፡ ራስ ወዳድ ነህ፣ ለእኔ ብቻ ለእኔ ብቻ ነው የምትለው፣ ጓደኛህን አታስቀድምም ስስታም ነህ" እያለ የነገር ናዳውን አወረደበት፡፡ ጓደኛ ውም ዓሣውን መብላቱን ቆም አደረገና፣ "ቆይ እስቲ እሺ አንተ ብትሆን የትኛ ውን ዓሣ ነበር የምትበላው?" ቢለው፣ "ትንሹን" አለ፡፡ በዚህ ጊዜ፣ "ታዲያ ምን ያስቆጣሃል፣ የቀረውስ ትንሹ አይደለም ወይ ለምን እርሱን አትበላም?" ብሎት አረፈው፡፡»

አዎ፣ ወገኖቼ፣ «ከእኔ ይልቅ ወንድሜ» የሚለውን ግሩም አመለካከት በተግባር እንጂ በአፋችን ብቻ አንግለጸው፡፡ ሁልጊዜም የእኛን ጥቅም ብቻ ለሚያመጣ ነገር ራሳችንን አንስጥ፣ ለባልንጀራችንም ጭምር እንጂ፡፡ እግዚአብሔርም ይርዳን፡፡

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፣
ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ!!» (ፊልጵ. 2፡4)፡፡

ግጥምጥም፡- ለእኔ ለእኔ ማለት ስስቴ ይብቃና፣
ወንድሜን ላስቀድም ልሁን ከእርሱ ኋላ፡፡

ያዕ. 2:14-17
1ኛ ዮሐ. 3:17

# አምስቱ ካልሲዎች!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ» (ገላ. 6:2)::

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው እርስ በርሱ እየተረዳዳና እየተደጋገፈ ፈጣሪውን በንጹሕ፣ ግብዝነትና ከንቱ ትምክህት በሌለበት አኳኋን እንዲያመልከው ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ዛሬ ግን እየኖርን ያለነው ምናልባት ከዚህ የራቀ ይሆን? እርስ በርሳችን እንደ ቃሉ ፍቅር ሊኖረንና ልንተሳሰብ ይገባል:: ሰውን ማትረፍ የሚቻለው በፍቅር ሥራ ነውና? ይህንን ከማድረግ አንጉደል:: ክርስቶስ እኛን ገንዘቡ ያደረገን ራሱን በመሠዋት የፍቅር ሥራ በመስቀል ላይ ሠርቶ ነውና እኛም የእርሱን ፈለግ ተከትለን ዋጋ በመክፈል ወንድማችንን ገንዘብ ማድረግ እንድንችል ጌታ ይርዳን» ለሚለው መልእክታቸው በወጣትነት ዘመናቸው የገጠማቸውንና በድል ያለፉትን ታሪክ እንዲህ ብለው ተናገሩ::

«ትዳር ከመመሥረታችን በፊት የቤት ኪራይ እንዲቀንስልን ሦስት ጓደኛ ሞች አብረን በጋራ ቤት ተከራየን:: በጥሩ ሁኔታ እየኖርን ሳለ በመካከላችን ግን አንድ ችግር እየጎላ መጣ:: ከሦስታችን አንደኛው ወንድም ካልሲውን አያጥብምና ቤቱ መሽተት ልማዱ ሆነ:: አምስት ካልሲዎች ስላሉት በየተራ ያደርጋል፣ አንዱ ሲቆሽሽ ከአልጋው ሥር ይወረውርና ሌላውን ያደርጋል:: እንዲህ እያለ የአምስቱን ካልሲዎች ዙር ሲጨርስ የመጀመሪያው ካልሲ ደርቆ ይጠብቀዋል:: እንደገና ሳይታጠብ ለሁለተኛ ዙር ይደረጋል:: እንዲህ እያለ አምስቱንም ካልሲ ያደርጋል:: በአጭሩ እኛ ቤት ሰው ሲመጣ ከሞተ ከአንድ ሳምንት የሆነው ድመት ያለ ይመስላል - ግማቱ:: በዚህ ጊዜ ሁለታችንም ተማከርን:: "ጥለነው ወጥተን ሌላ ቤት ብቻችንን ከምንከራይ እና ወንድማችንን ከምናጣው ለምን ካልሲውን አናጥብለትም" ተባባልን:: ማታ እርሱ ከተኛ በኋላ የመጥረጊያ ጉራጅ እንጨት ይዘን ከአልጋው ሥር ያሉትን ካልሲዎች ከየአድራሻቸው ከሰበሰብን በኋላ አጥበን ውጭ አሰጣን:: ጠዋትም እርሱ ሳይነሣ አምስቱንም ካልሲዎች ራስጌው አጠገብ ያለችው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥን:: እርሱም ከመኝታው በሚነሣበት ጊዜ ሁሉም ካልሲዎች "ዜግነታቸውን ቀይረውና" አምሮባቸው ተመለከተና ምንም ሳይናገር አራቱን ሳጥኑ ውስጥ ከቶ፣ አንዱን አድርጎ ሄደ:: ማታ ከሥራ ሲመጣ የመጀመሪያ ተግባሩ ካልሲውን አውጥቶ ማጠብ ሆነ:: እንዲህ አድርገን ወንድማችንን ገንዘብ አደረግነው:: በቤታችንም በጥሩ መዓዛ በእረፍት መኖር ጀመርን::»

አዎ ወገኖቼ፣ ወገናችንን ገንዘብ ማድረግ የምንችለው እርሱን ከነሸክሙ በመግፋት ሳይሆን ዋጋ ከፍለን ዝቅ ብለን ሸክሙን፣ ችግሩን፣ ረሃቡን በመጋራትና በማገዝ ነውና ይህንን እንድናደርግ ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- ይልቁን ልሸከም የወንድሜን ሸክም፣
በጉድፉ ምክንያት ዓይኑን ማውጣት ላቁም::

| |
|---|
| ዮሐ. 13:34-35፤ 15:12 |

# ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራል!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው» (1ኛ ዮሐ. 1:3)::

መጋቢው፣ «እግዚአብሔር ሲፈጥረን በኅብረት፣ በመስማማትና በአንድ ልብ ሆነን እንድናመልከውና እንድናገለግለው ነው እንጂ፣ በተለያዩ በራሳችን ሥጋዊ ምክንያቶች ተለያይተን የጎሪጥ እየተያየን እንድንኖር አይደለም:: ዛሬ ሰይጣን የተባረከውን ኅብረታችንን ለማፍረስ ብዙ መንገዶችን እየተጠቀመ ነው፤ ቋንቋችንን፣ ስማችንን (ዝናችንን)፣ ውበታችንን፣ ዘራችንን፣ አገራችንን ሁሉ አጉልቶ በማሳየት ለዚህ ዋጋ ለሌው ግሳንግስ ነገር ዋጋ ሲያስከፍለን ይታያል:: በዚህ እግዚአብሔር አይከብርምና ሰውን ሁሉ በክርስቶስ አውቀን ክብራችንን፣ ዝናችንን፣ ቋንቋችንን እና ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ለእግዚአብሔር በማስገዛት በኅብረትና በፍቅር ልናመልከውና ልናገለግለው ያስፈልጋል:: በቀጣዩ ሕይወታችን የእኔነትን መንፈስ አስወግደን በጋራ እየገፋ ያለውን፣ አገሪቱን ድንበራችንን በራሱ ለማድረግ ሌት ተቀን በዐመፅ አሠራሩ ደፋ ቀና የሚለውን ጠላታችንን ልንመክትና ብሎም ልናጠፋ ይገባናል» ለሚለው መሠረታዊ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«ሰባት ልጆች ያሏቸው አንድ አባት በሞት አፋፍ ላይ ሆነው ልጆቻቸው ሁሉ እያንዳንዳቸው አንድ አንድ አርጩሜ ይዘው እንዲመጡ አዘዙ:: ከመጡ በኋላ ሁሉም ያመጡትን አርጩሜ በእርሳቸው ፊት በጉልበታቸው እንዲሰብሩ አዘዙ:: ሁሉም የራሱን ሰበረ:: እንደገናም ሌላ ሰባት አርጩሜ እንዲያመጡ አዘዙ:: አርጩሜ ማመላለስ ሊሞት ለሚያጣጥር ሰው ጥቅሙ ምን እንደሆነ ምሥጢሩ ባይገባቸውም፣ አሁንም የአባታቸውን ፈቃድ ለመሙላት ሄደው አመጡ:: አሁን አባታቸው እንዲህ አሉአቸው:: "ሰባቱንም በአንድ ላይ እሠሩና አንዳችሁ በጉልበታችሁ ለመስበር ሞክሩ::" እንደተባለው ለማድረግ ሞከሩ፣ ግን መስበር አልቻሉም:: በዚህ ጊዜ አባታቸው፣ "እያችሁ፣ ልጆቼ ለእናንተ ያለኝ የመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ይህ ነው:: ጠላትን በተናጠል ማጥቃት አትችሉምና ኅብረት ይኑራችሁ:: ልጆቼ ስሙ፣ ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራልና ተባበሩ፣ ተያያዙ፣ ተዋደዱ፣ ተጠያየቁ፣ ተነፋፈቁ፣ ያን ጊዜ በጠላት ወረዳ ላይ የበረታችሁ አሸናፊዎች ትሆናላችሁ::"»

አዎ፣ እኛም ሰው ከሰው ሳንለይና ሳንለያይ ሰው ሁሉ በውስጡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንዳለበት ተረድተን፣ ለዚህም ሰው እግዚአብሔር ቋንቋውን እና ዝርያውን የሰጠው ለመግባቢያና ለመለያ መሆኑን አውቀን ቤተ ክርስቲያን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራርበን፣ መሪ ከመሪ ጋር ተያይዘን በኅብረትና በአንድነት እግዚአብሔርን ልናገለግል ይገባናል:: ይህ ከሆነ ሽንፈት ለጠላት፣ ድል ለሕዝቡ ይሆናል:: ቀሪው ዘመናችን የኅብረት፣ የአንድነትና የፍቅር ይሁንልን:: አሜን!

ግጥምጥም:- በኅብረት ለኅብረት ለፈጠረኝ ጌታ፣
ራሴን ሳስገዛ፣ ለምን ልንገላታ::

ዮሐ. 3:17-11
ፊልጵ. 2:1-2

# ፍቅር እውር ነው

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወድዳል» (ምሳሌ 17:17)::

የታደሙት ሰዎች አዳራሹን ግጥም አድርገው ሞልተውታል:: ከፊት ለፊት ከሰባኪው ትይዩ የዕለቱ ሙሽሮች በክብር ልብሳቸው ተሰይመው፣ በሚዜዎቻቸው ታጅበው ጎልተው ይታያሉ:: የዕለቱም ሰባኪ ከፍ ባለ ድምፃቸው እነርሱንና ጉባኤውን ከእግዚአብሔር ቃል ያስተምራሉ:: «ፍቅራችሁ ጊዜያዊና ወረት የዳሰሰው አይሁን:: እውነተኛ ወዳጅ በሁኔታዎች አይለወጥም:: ዛሬ ብዙ ሰዎች ፍቅራቸው ከሚጠፋ ነገር ጋር የተያያዘ ነው:: የሚጠፋው ነገር ሲጠፋ ወዳጅነታቸውም ይጠፋል:: ዛሬ ከአንዱ ወዳጅነት ይጀምራሉ፣ ነገ አቋርጠው ወደ ሌላው ይሄዳሉ:: ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው:: ፍቅራችሁ እስከወዲያኛው ይዝለቅ» እያሉ ያስተምራሉ:: ይህንን ትምህርት በምሳሌ አስረግጠው ሲናገሩ እንዲህ ይሉ ነበር::

«በአንድ አካባቢ ወ/ሮ አየለች የሚባሉ ሴት አራት ፎቅ ያለው ቤት ጀመሩና እስከ አራተኛ ፎቅ ድረስ ለመጨረስ የገንዘብ አቅማቸው ስላልፈቀደ ከለሙን (ምሰሶዎቹን) ብቻ አቁመው ተዉት:: ለረጅም ዓመታት ሳይሠራ በመቅረቱ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ የታወቀ ሆነ:: እንዲያውም ይባስ ብሎ ነዋሪው እርስ በርስ ላለመከዳዳት ቃል ኪዳን ሲገባባ አንዱ የአንዱን እጅ ይይዝና፣ "እንደ አየለች ፎቅ ጀምሮ ያስቀረኝ አልክድህም" እያለ መማያ አደረገው::»

አዎ፣ እኛስ ዛሬ ከአንዷ ጋር ጀምረን ዓመት ሳይሞላ ነገ ከሌላዋ ጋር እያልን «እንደ አየለች ፎቅ» ጀምረን የተውነው ብዙ የፍቅር ዕዳ ይኖርብን ይሆን? እንመለስ ወይም ይህንን ሥራችንን እንተው:: እውነተኛ ፍቅር ሙሉና ዘላቂ ነው፤ ጎደሎ አይደለም:: «ፍቅር እውር ነው» እንደሚባለው ሳይሆን ፍቅር ዐይናማና ሙሉ ነው:: ሁኔታን አይቶ አይለወጥም፣ ወይም በሁኔታዎች አይቀየርም:: ፍቅር የራሱን አይፈልግም:: በግብዝነትና በወረት የታጀበን ፍቅር አስወግደን በእውነትና በንጹሕ ልብ እርስ በርሳችን ተዋደን እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆናችንን ለዓለም በመመስከር ዘመናችንን እንድንፈጽም ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ፍቅር ዕውር ነው ለምን ትላላችሁ፣
ፍቅር ዐይናማ ነው እዩ አስተውላችሁ::

| |
|---|
| ሉቃ. 10:29-37<br>1ኛ ቆሮ. 13:4-8<br>ዮሐ. 13:35 |

# ከእኔ በላይ ላሳር

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን...» (ሮሜ 12:6)

በየዓመቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለአገልጋዮች በምታዘጋጀው የአገልጋዮች የትምህርት ጊዜ ላይ ተገኝተው መጋቢው እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ:- «አገልጋዮች በተሰጠን ጸጋ መሠረት እያገለገልን የሌላውንም ጸጋ ልናከብር ይገባናል እንጂ በቅንአትና በምቀኝነት የሌላውን ጸጋ ማንቋሸሽ የለብንም:: ጌታ ለሁላችንም የተለያዩ ስጦታ የሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና ክብር እንጂ ለራሳችን አይደለምና ክብር ለራሳችን በመውሰድና በመኩራስ ከእኔ በላይ ላሳር ማለት የለብንም:: በሁሉም ሰዎች ላይ እግዚአብሔር የሚጠቅም የጸጋ ስጦታ እና ብቁ ችሎታ ሰጥቷልና በየትኛውም ሰው ይሁን በየትኛውም የጸጋ ስጦታ አገልግሎት ይህኛው ከዚህኛው ይበልጣል፤ ያንሳል የምንለው መኖር የለበትም::» ለዚህ ግሩም ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«አገርን በመጎብኘት ላይ ያሉ አንድ ፈላስፋ ትልቁን ወንዙ በጀልባ እያሻገራቸው ላለው ገበሬ እንዲህ እያሉ ጥያቄ መጠየቅ ጀመሩ:: "እኔ የታወቅሁ ፈላስፋ ነኝ፣ ብዙ ታዋቂነት በዚህች ዓለም ላይ አለኝ፣ ብዙ ሥራዎችንም በችሎታዬ ሠርቻለሁ:: ለመሆኑ አንተ የምትታወቅበት ሥራ ምንድን ነው?" ቢሉት፣ "ምንም" አለ:: "የእድሜህን ግማሹን አልኖርክማ" አሉት:: አሁንም ሌሎችም የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠየቁት፤ እርሱም ምንም እንዳልሠራ በነገራቸው ጊዜ ሁሉ እየደጋገሙ በተከታታይ፣ "የዕድሜህን ግማሹን አልኖርክማ" እያሉ ሲሉት መጨረሻ ላይ ተበሳጨና ከወንዙ መሐል ላይ እንዳሉ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፣ "ጌታዬ፣ አሁን ለምሳሌ ከፊታችን ይህችን ጀልባ ሊገለብጥ የሚችል ማዕበል እየመጣ ነው:: እኔ ዋና እችላለሁ፣ ለመሆኑ እርስዎስ ዋና ይችላሉ?" አላቸው:: በዚህ ጊዜ ፈላስፋው እያፈሩና እየተደናገጡ፣ "አልችልም" አሉት:: ገበሬውም በመደሰት፣ "በቃ ከእንግዲህ በኋላ የዕድሜዎን ግማሹን አልኖሩትም" ብሎ መለሰላቸው ይባላል::»

አዎ፣ እንዳችን ውስጥ የሌለው ስጦታ በሌላችን ውስጥ አለና እየተደጋገፍንና እየተመካከርን በቀና እና በመቀባበል መንፈስ እናገልግል እንጂ እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ:: ይልቁንም በትሕትናና በተዋረደ መንፈስ የስጦታውን ባለቤት እግዚአብሔርንና የእርሱን ሕዝብ እንድናገለግል ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ስጦታው የእግዚአብሔር መሆኑን አውቁ፣
ከወንድሜ ጋራ ልኑር ተጠንቅቁ::

| |
|---|
| ሮሜ 12:3-5 |
| ሮሜ 12:10 |

## ክፍል 3
## እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን

# ወንደላጤውና ድመቷ

ሰባኪው፣ «መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያለ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁላችን ሁሉን እንመረምራለን እንጂ በማንም አንመረመርም:: ስለሆነም በዚህ ምድር ላይ በሕይወታችን ላይ በሚገጥሙን መሰናክሎች ወይም አለመሳካቶች ላይ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ፈቃዱ ምንድን ነው ብለን መመርመር፣ መጸለይ እና ማስተዋል አለብን እንጂ ገና ከመጀመሪያው ተስፋ ቆርጠን መቆዘም የለብንም:: ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከደረሰብን ክፉ ነገር ባሻገር መልካም ነገር እንዳለ እናስብ:: ከትኃሚን ኪሣራ ሩት እንደ ወጣች ሁሉ፣ ከእኛም ኪሣራ (ጉዳት) መልካም ነገር ይገኛል:: እግዚአብሔር በመጀመሪያ መጨረሻውን ያውቃልና ሁልጊዜ በደረሰብን ነገር ሁሉ እናመስግን እንጂ አናጉረምርም፤ በመጨረሻው ፈውስ፣ በረከት፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ጸጥታና ሕይወት ነውና» ለሚለው ግሩም ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

የገናን በዓል ለማክበር ሁሉም ሰው ከቤተሰቡ ጋር ምንም ሳይጎድል ቤቱን ሞቅ አድርጎ ለመዋል በጉን፣ ዶሮውንና፣ ቅርጫውን ለማስገባት ይሯሯጣል:: አንድ ትዳር ያልመሠረተ ወንደላጤም እኔስ ከማን አንሼ በማለት ቅርጫ ገባና ሥጋውን በዘንቢሉ ወደ ቤቱ ይዞ ገብቶ አንድ ሙዳ ጠብሶ ለመብላት መክተፊያው ላይ አስቀምጦ ቢላዋ ለማምጣት ወደ ጓዳ ሲገባ፣ አንዲት ድመት ገብታ ያንን ሙዳ ሥጋ በአፈር ላይ እየጎተተች ወደ ውጭ ይዛ ትወጣለች:: ወንደላጤው ቢላዋ ይዞ ከጓዳ ሲወጣ ሙዳ ሥጋው የለም:: ወደ ውጭ ሲመለከት ድመቷ ትጎትታለች:: በጣም ተበሳጭቶ በያዘው ቢላዋ የዘራችውን ሊያሳጭዳት ተከትሎ ሲሮጥ ሥጋውን ይዛ ጢሻ ውስጥ ገባች:: በዚህ በጣም ተናዶ ወደ ቤቱ ሲመለስ፣ የቤቱ ጣራ እንዳለ ተደርምሶ ቤቱ ወድቋል:: በዚህ ጊዜ ወንደላጤው የቤት ፍርስራሽ ተጭኖት ታፍኖ አለመሞቱን እያሰበ እንዲህ አለ:: «ለካ አምላኬ ድመት ልኮ ሥጋዬን ያስወሰደው፣ እኔን ከቤት አውጥቶ ሥጋዬን ለማዳን ነው» ሲል አምላክን አመሰገነ::

አዎ፣ ሁልጊዜ የነገሮቻችን መጀመሪያና መጨረሻ አንድ አይሆንምና እናስተውል:: እግዚአብሔር በራሳቸው በጎ ያልሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለበጎ መለወጥ ይችላልና አሁን ያለንበትን መጥፎ ሁኔታ እግዚአብሔር መጨረሻውን ወደ መልካም ያመራና በረከት ያለበት ያደርገዋልና እርሱን እንጠብቅ:: ይህንንም እንድናስተውል እግዚአብሔር በጸጋው ይደግፈን:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም» (ኤር. 29:11)::

ግጥምጥም:- አምላኬን ልጠብቅ ምንም ነገር ቢሆን፣
እንደ መጀመሪያው መጨረሻው አይሆን::

| |
|---|
| ኢዮብ 42:2 |
| መዝ. 107:13 |

# ሠላሳ - ሁለት ጥርስ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና» (1ኛ ተሰ. 5:18)::

መጋቢው፤ «የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእኛ ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ፣ ቃሉ "በነገር ሁሉ እያመሰገናችሁ እንድትኖሩ ነው" የሚል ግልጽ የሆነ ምላሽ ይሰጠናል:: የእኛ ተግባራዊ ምላሽ ታዲያ በነገር ሁሉ ከማመስገን ይልቅ ማጉረምረም ይሆን? ሰይጣን፣ ከሆነልን ይልቅ የሆነብንን አጉልቶ ያሳየንና ከምስጋና ይልቅ አጉረምራሚዎች እንድንሆን ያደርገናል:: የእግዚአብሔር ቃል ግን፣ "በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ" (ፊልጵ. 4:6) ይላል:: ወገኖቼ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገው ትውልድ ሲሆንለት ብቻ ሳይሆን ሳይሆንለትም የሚያመሰግን፣ ሲሞላ ብቻ ሳይሆን ሲጎድልም የሚያመሰግን፣ በነገር ሁሉ በምስጋና የተሞላን እንጂ በነገር ሁሉ በማጉረምረም የተሞላን አይደለምና እስኪ ለምስጋና እንነሣ:: በምስጋና ድል ይገኛል:: የሚያመሰግን ሕዝብ ሩጫውን ይጨርሳልና በነገር ሁሉ ጌታ ሁላችንንም አመስጋኞች ያድርገን» ለሚለው ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

ከሠላሳ ሁለት ጥርሳቸው ሁለት ጥርስ ብቻ የቀራቸው አሮጊት በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ከጎኑ ቁጭ ብለው ሲያመሰግኑ የሰማቸው ወጣት ከጸሎቱ ፕሮግራም በኋላ፣ «እኔ ሠላሳ ሁለቱም ጥርሴ ግጥም ብሎ እያለ አንድ ቀን ትዝ ብሎኝ አመስግኜ አላውቅም፣ እርስዎ ግን ሠላሳውን አጥተው በሁለቱ ብቻ የሚያመሰግኑበት ይህ ምሥጢር ምንድን ነው?» ሲል ገርሞት ጠየቃቸው:: አሮጊቷም እንዲህ ሲሉ መለሱ፣ «ልጄ፣ እኔ የማመሰግነው እኮ ሁለት ጥርስ ስላለኝ ብቻ ሳይሆን፣ መንከስ እንዲችሉ አንዱን ከላይ አንዱን ከታች ስላደረገልኝም ጭምር ነው» ብለውት አረፉ::

አዎ፣ ወገኖቼ ሆይ፣ እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ እናመስግን ካልን ያለንን እንቁጠር፣ በሁሉም እርሱን እናመስግን:: አሁን የሆንነውን የሆንነው ከጌታ ምሕረትና ጥበቃ፣ ከቸርነቱም የተነሣ ነውና በነገር ሁሉ እርሱን አመስግነን ጠላትን ማሳፈር እንድንችል ጌታ ይርዳን:: አሜን::

| |
|---|
| መዝ. 92:1 |
| መዝ. 118:1 |

ግጥምጥም:- ሲሞላ ማመስገን ሲጎድል ማማረር፣
ይበቃል ይቋረጥ እንዲህ ያለ ነገር::

# ክፍል 4

# ለእግዚአብሔር ስለ መኖር

## የኃለሞታ ልብስ

ሰባኪው: «ዛሬ የምናገረው መልእክት ለምንሰማው፣ ለምናየውና ለምናደርገው ነገር ሁሉ ጥንቃቄ እንድንወስድ ነው:: ኃጢአት በዓይንና በጆሮ ገብቶ ነውና ልብን የሚለውጠው፣ በየቀኑ ለምንሰማውና ለምናየው ልንጠነቀቅ ይገባል:: ሔዋን ፍሬው ለመብላት እንደሚያስጎመጅ አይታ ነው በኃጢአት የወደቀችው:: ዳዊት ቤርሳቤህ ስትታጠብ አይቶ ነው በኃጢአት የወደቀው:: ስለዚህ እኛም ሆነን ቤተሰቦቻችን ለምናየውና ለምንሰማው ልንጠነቀቅና ልናስጠነቅቅ ይገባል:: የማየትና የመስማት ኃጢአት ወደ ተግባር ለመውሰድ ኃይል አለው:: በተለይም በአሁን ሰዓት ሰይጣን ክርስቲያኖችን እየጣለ ያለው በዝሙት ነው:: ለዚህ የሚጠቀምበት አቋራጭ መንገዱ የዝሙት ፊልም በማሳየት እና የኃለሞታ ልብስ በማልበስ ነውና እኛም ሆነን ልጆቻችን የምናያቸውን ፊልሞች እንመርምር:: በተለይ እግዚአብሔር የሰጠንን ልጆች እንደ እግዚአብሔር ቃል ቀርጾ አሳድጎ ለእግዚአብሔር ሠራተኞች እንዲሆኑ የማብቃት ኃላፊነት አለብንና:: ወላጆች ልጆቻችንን ብዙ አንራቅ፤ የሚያነቡት፣ የሚያዩትና የሚሰሙት ሁሉ ጽድቅን የሚያሳይ መሆኑን እንይ፣ እናሳይ፣ እንመርምር፤ ካልሆነም እንመለስ:: በአጠቃላይ ሰይጣን ዛሬ እኛን ወደ ኃጢአት ለማስገባት ቴክኖሎጂውንም እየተጠቀመ ነውና የምናየውን ቴሌቪዥን፣ የምናነበውን ጋዜጣ፣ የምንላላክበትን ኢንተርኔት እና የምንሰማውን ሬድዮ ሁሉ ልንመረምር ይገባል:: ፍሬውንም ከገለባው ለይተን ልንወስድና በሕይወታችን እግዚአብሔርን ልናከብር ይገባል» ለሚለው የጊዜው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ::

«እድሜያቸው ከመግፋቱ የተነሣ እቤት የዋሉትን እናቱን ማገላበጡ፣ ማውጣት ማግባቱ፣ ማቅናት ማስተኛቱ እጅጉን አድክሞታል:: ብቻውንም ስለሆነ በጣሙን አሰልችቶታል:: ታዲያ በዚህ ሁኔታ እያለ አንድ ሰው ሊፈትነው ወደ እርሱ መጣና፣ "እናትህን ትሸጣለህ ወይ?" ብሎ ጠየቀው:: በጣም የደነገጠውም ልጅ፣ "እናቴን ያሳደገችኝን! ምን ዓይነት ሰይጣን ነህ? በል ሂድ ከአጠገቤ" ይልና ያባርረዋል:: ትንሽም ሲያስብ ሲያሰላስል በጆሮው የሰማው ቃል ወደ ልቡም ሄደና ይስተናገድ ጀመረ:: ገንዘብ ካወጣች ለምን አትሸጥም አለና ሮጦ በመከተል ሰውዬውን ጠርቶ፣ "ለመሆኑ ስንት ታወጣለች?" ብሎ ጠየቀ::»

አዎ፣ የምናየውና የምንሰማው ቃል ውስጣችን ገብቶ የመለወጥ ኃይል አለውና ለምንሰማውና ለምናየው ሁሉ አብዝተን ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል:: ጌታም ለሁላችን ማስተዋሉን ይስጠን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ልጄ ሆይ፣ ወደ ጥበቤ አድምጥ ጆሮህን ወደ ትምህርቴ መልስ::» (ምሳሌ 5:1)

> «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ»
> (ኢዮብ 31:1)

# አልማዝ ባለጭራ

መጋቢው፣ «በምድር ላይ ብንኖርም የተጠራነው "የሰማያዊ ኑሮ" እንድንኖር ነው እንጂ የምድራዊ ኑሮ እንድንኖር አይደለምና እግዚአብሔርን የማያስከብሩ ምድራዊ ምኞቶቻችንን ልንገድል ይገባል:: ዛሬም በምድራችን ኤች አይ ቪ/ ኤድስ፣ ሳርስ፣ አልማዝ ባለጭራ እያልን ስም የምንሰጣቸው ወረርሽኞች ሁሉ የመጡብን ክፉ ምኞቶቻችንን ማለት ዝሙትን፣ ርኩሰትን፣ ጣዖት ማምለክን፣ ሌሎችንም ስለአልገደልንና በንጽሕናና በቅድስና ስሙን ከሚጠሩት ጋር ስለአልተባበርን ነው:: ስለዚህ ዛሬ መልእክቴን የምትሰሙ እናንተ ሁላችሁ አሮጌውን ማንነታችንን ወይም አሮጌውን ሰው አስወግደን አዲሱን ማንነታችንን እርሱም ክርስቶስን እንልበስ:: እግዚአብሔር "ግደላቸው"፣ "አጥፋቸው"፣ "ምታቸው" ያለንን የማይጠቅሙንን ባሕርይዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ እናጥፋ እንጂ እየቀናነስን አናድርግ:: ፈጽሞ መግደል ያለብንን አሁኑኑ እንግደል::» ይህንን መልእክት ሳዘጋጅ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸመ ድርጊት ትዝ አለኝ::

«ጊዜው የፋሲካ ሰሞን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ በውስጧ ለሚገኙ ችግረኞች በሬ ገዝታ ሥጋ ለማከፋፈል አሰባለች:: በዕለቱም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ይህንን ኃላፊነት ይወስዱና በሬው ተጥሎ ይታረዳል:: ነገር ግን በሬውን የሚያርዱ አራጆች ብዙ ልምድ የሌላቸው ኖሮ፣ ታርዷል ተብሎ የተገመተው በሬ ለካ ጉሮሮው አልተቆረጠም ነበርና ድንገት ተነሥቶ ደሙን እያዘራ በግቢው ውስጥ መሮጥ ጀመረ:: በዚህ ጊዜ አገልጋዮች ሁሉ እየተከተሉ "በኢየሱስ ስም! በኢየሱስ ስም" እያሉ መገሠጽ ጀመሩ::»

አዎ ወገኖቼ፣ መጀመሪያውኑ መግደል ሲገባን የእኛን ኃላፊነት ሳንወጣ የጌታን ስም ለመጥራት አንቸኩል:: ጌታ በቃሉ በምድር ያሉ ምድራዊ ብልቶቻችሁን ግደሉ ነው ያለው እንጂ እኔ እገድልላችኋለሁ አላለምና የእኛን ድርሻ እንወጣ:: አራጆቹ በያዙት ቢላዋ በሬውን እስከ መጨረሻው ማረድና መግደል እንደ ነበረባቸው ሁሉ፣ እኛም በተሰጠን ቃል፣ በመንፈሱና በጸሎት እግዚአብሔርን የማያስከብረውን በውስጣችን ያለውን ዓለማዊ ባሕርያችንን እንድንገድል ጌታ ይርዳን:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እንግዲህ በምድር ያሉ ብልቶቻችሁን ግደሉ እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት ፍትወት፣ ክፉ ምኞት፣ ጣዖትን ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው» (ቆላ. 3:5)::

| |
|---|
| ቆላ. 3:8-9 |
| ኤፌ. 5:3 |

ግጥምጥም:- «በምድር ላይ ኖሬ ምድራዊ እንዳልሆን፣
አዲሱን ሰው ልብስ ሳውልቅ አሮጌውን::

# ሴትን ክጃለሁ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ፣ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ» (ዮሐ. 8:11)።

ሰባኪው፣ «ዛሬ ሕይወታችንን እያቀጨጨ ያለው ምንድን ነው? ለሚለው የብዙዎቻችን ጥያቄ ምላሹን ይገኘ መጥቻለሁ። ይኸውም ለዚህ ያበቃንን ኃጢአት ከሥር ከመሠረቱ መንግሎ በማውጣት መካድ ነው። በሚቀጥለው አዲስ ዓመት እንዲህ እሆናለሁ ወይም አደርጋለሁ ብለን አዲስን ነገር ለእኛና ለቤታችን ተመኝተን አዲሱ ዓመት አሮጌ ሆኖ ሲያልቅ ግን ምኞታችን ሁሉ የውኃ ሽታ ሆኖ እንዳምናው ዘንድሮም ሕይወታችን ያው የሆነው ለምንድን ነው? የልምምድ ኃጢአታችንን እስከ መጨረሻው ስላልካድን ነው፣ ወይም ስላላወቅን ነው፣ ወይም ብንክድም ክህደቱ ከልብ አልነበረምና ተመልሰን በዚያው ኃጢአት ተይዘን ነው። ወገኖች፣ ዛሬ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን በጌታ ፊት ስንገዝ «ምንም አይደለም» እያልን የምንሠራቸው ጥቃቅን ኃጢአቶች ሁሉ በጌታ ፊት ጎልተው ሕይወታችንን እያቀጨጩት፣ እንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን እየበረበሩን ይገኛሉና ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምደን በመያዝ አላሳድገንና ከጌታ ጋር አላገናኝን ያለውን አንቆ የያዘንን የልምምድ ኃጢአታችንን አሁን ልንክደው ይገባል» ለሚለው መሠረታዊና ግሩም ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«ቤተ ክርስቲያኒቱ ባዘጋጀችው ዓመታዊ ታላቅ የወንጌል ስርጭት ኮንፈረንስ ላይ የደኅንነት የወንጌል ስብከት ሰባኪው ከሰበኩ በኋላ ጥሪ ሲያቀርቡ፣ "ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣችሁ ብትኖሩ ከዘላለም የገሃነም እሳት መዳን የሚቻለው ስለ እኛ በሞተው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነውና አሁን እጸልይላችኋለሁ፣ እየተነሣችሁ ወደ ፊት ኑ" አሉ። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው በፍጥነት ከመቀመጫቸው ተነሥተው ወደ ሰባኪው መጡ። ሰባኪውም፣ "እኔ የምለውን ከእኔ ቀጥለው በማለት ንስሐ ይግቡ" ብሏቸው እንዲህ እያለ ቀጠለ። "ጌታ ኢየሱስ ሆይ"፣ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ"፣ "አንተን አምናለሁ።" "አንተን አምናለሁ።" "ዓለምን ክጃለሁ፣" "ዓለምን ክጃለሁ፣" "ሰይጣንን ክጃለሁ፣" "ሴትን ክጃለሁ"፤ በዚህ ጊዜ ሰባኪው "ሰይጣንን ክጃለሁ በሉ ነው ያልኩት እንጂ ሴትን ክጃለሁ አላልኩም" ቢላቸው። "እባክህ ተወኝ፣ በዝሙትዋ ቀላልፋ ከጌታዬ ጋር አላገናኝ ያለችኝን ጠላቴን እኔ አውቃለሁና ጸሎትህን ቀጥል" ብለውት አረፉ።»

አዎ ወገኖቼ፣ ሁሉ ጊዜ ሕይወታችንን እያቀጨጨ አላሳድግ ያለንንና ከጌታችን ጋር ያለንን ኅብረት የሚያሻክርብንን የልምምድ ኃጢአት ማወቅ አንድ ድል ነው። ዛሬ ለዘላለም እንካደው። ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ደግመን እንዳናደርገው አምላክ ይርዳን። አሜን።

| |
|---|
| ሉቃስ 3:7-9 |
| ያዕ. 5:16 |

ግጥምጥም:- የልምምድ ኃጢአት ሕይወቴን ጎድቶታል፣

ክጃለሁ ከእንግዲህ አምላኬ አይቶታል።

# ክፍል 5
## ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት
## ሰይጣንን በቆመጥ

የቃል ጥቅስ:- «እነሆም፣ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» (ሉቃ. 24:48)::

ሰባኪው፣ «ማንም ሰው ከላይ በሚያገኘው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ ከታች በሚያገኘው የሥጋ ኃይል ሰይጣንን ሊያሸንፍና በአገልግሎቱ የተሳካለት ሊሆን ፈጽሞ እንደማይችል አገልጋዮች ሁላችን ይህንን ማወቅና ለዚህም መገዛት አለብን:: ለዚህ ነው ቃሉ፣ "ማንም ሰው ሲያገለግል እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ይበል::" (ሉቃስ 17:10) ተብሎ የተጻፈው:: ደቀ መዛሙርት ከሰማይ ጌታ በላከላቸው ኃይል ሮጡ፣ ግን አልደከሙም፤ ተፍገመገሙ፣ ግን አልወደቁም፤ ወንጌልን ሰበኩ፤ እስከ ሞት ድረስም የታመኑ ሆኑ:: እኛስ ዛሬ የምናገለግለው በማን ኃይል ነው? በማንስ እውቀት ነው? መማር፣ ማወቅና የብዙ ዲግሪዎች ባለቤት መሆን ግሩም ነው:: ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል ካላስገዛን ውጤቱ ያማረ አይሆንም:: ለእኛ ለክርስቲያኖች ያለን ጠላት በሥጋ ኃይል የሚረታ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚሸነፍ መሆኑን ማወቅ በራሱ ድል ነው::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በከተማው እምብርት ባለው ስቴዲዮም ላይ ታላቁ ኮንፈረንስ መካሄዱን ቀጥሏል:: መዘምራኑ ከዘመሩ በኋላ ሰባኪውም በጌታ ድንቅ ኃይል ስብከታቸውን ሰበኩ:: በመጨረሻም የደኅንነት ጥሪ ካደረጉ በኋላ ለበሽተኞች ሲጸልዩ በሽተኞች መፈወስ ጀመሩ:: አጋንንት ከያሉበት እየጮኹ መውጣት ጀመሩ:: ስቴዲዮሙ በቅዱሳንና በርኩሳን ጩኸት ተደበላለቀ:: በዚህ ጊዜ መድረኩ አካባቢ ለአስተናጋጆች ያስቸገረውን፣ አጋንንት ያደረበትንና የያዙትን ሰዎች ለመማታት የሚወራጨውን አንድ ወጣት በጊዜው የስቴዲዮሙን ጸጥታ ለመጠበቅ ከተሰማሩት ፖሊሶች አንዱ አየውና ተንደርድሮ ሄዶ በያዘው ቆመጥ ሁለት ጊዜ ሲመታው ሰባኪው አዩና እንዲህ አሉ:: <ተው በሥጋ ኃይል ርኩስ መንፈስን ልታስወጣ አትችልም:: ሰይጣንንም በቆመጥ ልታሸንፈው አትችልምና ወደ እግዚአብሔር መንፈስ አምጣው> ብለው ጸለዩለትና ወጣቱ ነፃ ወጣ::»

አዎ ወገኖቼ፣የሥጋ ኃይል የመንፈስን ኃይል ሊቋቋም አይችልምና ወደ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል እንምጣ እርሱንም ታጥቀን በእኛ ያሉትን ሥጋዊ ቆመጦቻችንን አስወግደን እንድናገለግለው ጌታ ይርዳን::

| | |
|---|---|
| ግጥምጥም:- የእኔን ኃይል በኃይልህ ጌታ ግዛውና፣<br>ምርኮን ከጠላቴ ልበዝብዝ ልውጣና:: | የሐዋ. 1:8<br>1ኛ ጴጥ. 5:8 |

# መስተፋቅር በሎሚ

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር ስለ እኛ ይዋጋል። እግዚአብሔር ግን በጦርነቱ አሸናፊ እንዲሆን እኛ በቅድስናና በጽድቅ እርሱንም በመምሰል ልንኖር የግድ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል በሰይጣን ኃይል ላይ ጥሶ እንዲወጣ መውጣት መግባታችን እንደ ቃሉ እና እንደ መንፈስ ፈቃድ ሊሆን ይገባል። ይህ ከሆነ ሰይጣን ዲያቢሎስ በእኛ ላይ የሚያሴረው ሴራ ይከሽፋል፣ የለጠጠው ቀስቱም ይሰበራል። እግዚአብሔርም በልጆቹ ሕይወት ላይ ከፍ ብሎ በዚህች ዓለም ላይ ይከብራል።» ለሚለው ሕይወት ለዋጭ ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተናገሩ:-

በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የክርስቶስን ሕይወት በሕይወቷ የምትመሰክር ታማኝ ክርስቲያን ልጅ ነበረች። በሥጋም ውብ ነበረችና ብዙ ወንዶች ተማሪዎች ይሳቡባታል። ግማሹ ለጊዜው፣ ግማሹ ለዘለቄታ እንደሚወዷት ይገልጹላታል። እርሷ ግን ሁሉንም በቀና መንፈስ እንዲህ ዓይነት ዓላማ ለጊዜው እንደሌላትና ትምህርቷን ብቻ መማር እንደምትፈልግ ትገልጽላቸው ነበር። አንድ በግቢው በመጥፎ ባሕሪው የሚታወቅ ወጠምሻ ተማሪ ግን ጠንቋይ ቤት ሄዶ መስተፋቅር በሎሚ አስደግሞ አመጣና በጓደኛዋ በኩል ላከላት። ለጓደኛዋም እንዲህ ብሎ አስጠነቀቃት፣ «እነዚህ ሁለት ሎሚዎች ላንቺና ለጓደኛሽ ናቸው። እንደነገርኩሽ ይኸኛው ምልክት ያለበት ሎሚ መስተፋቅር የተደገመበት የእርሷ ሎሚ ነው። ይኸኛው ምንም ምልክት የሌለው ደግሞ ያንቺ ነው። አደራ ተሳስተሽ የእርሷን እንዳትበይና ጉድ እንዳትሠሪኝ።» ይላትና ይሰጣታል። እርሷም እሺ ትልና በእረፍት ሰዓት ለጓደኛዋ ሎሚ እንደገዛችላት ትነግራትና ትሰጣታለች። ይህችም አማኝ ልጅ ስላደረገችላት በጎ ነገር ጓደኛዋን እያመሰገነች በእጇ ሎሚውን ሳትመጠው ይዛው ሳለ ከእርሷ ጋር ሁልጊዜ ለመቀለድ የሚፈልግ አንድ ሌላ ተማሪ ከእጇ ላይ መንትፎ ይዞ ይሮጣል። በዚህ ጊዜ ያቺ ጓደኛዋ ምሥጢሩን ስለምታውቅ እየተከተለች መጮኽ ጀመረች፣ ኧረ መልስ፣ ተው እንዳትመጠው፣ አለበት፣ አለበት፣ እያለች።» ልጁ ግን ያለችውን ሳያስተውል፣» ይኑርበት፣ ይኑርበት» እያለ ሎሚውን መርጦ ጨረሰው።

አዎ፣ እግዚአብሔር በየዋህ ልጆቹ ላይና ያለ ነውርና ነቀፋ በቅድስና በሚመላለሱ ልጆቹ ላይ ሰይጣን የደገሰውን ድግስ እንዲህ አድርጎ ያከሽፋል። ዛሬም በአንተ ሕይወት ሰይጣን ብዙ ነገር ያደርጋል። ግን በበጉ ደምና በመልካም የሕይወት ምስክርነት ድል እንድትነሣው ጌታ ይርዳህ: አሜን

የቃል ጥናት ጥቅስ: «በያዕቆብ ላይ አስማት የለም፣

በእስራኤልም ላይ ምዋርት የለም» (ዘኁል. 23:23)

ግጥምጥም:- ጌታን እያከበርኩ እኔ ስመላለስ፣

እርሱ ያከሽፈዋል የጠላቴን ድግስ።

| |
|---|
| መዝ. 124:6 |
| ዘኁል. 23:21 |

# አጋንንቱና ሥራ አስኪያጁ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፣ ደስ ይበላችሁ።» (ፊልጵ. 4:4)

መምህሩ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎቻቸው ወደ ዕለቱ ትምህርት ከመሄዳችን በፊት አንድ ቃል ላካፍላችሁ ብለው ፊልጵ. 4:4 አንብበው እንዲህ አሉ።

«ጌታን በማመናችሁና በመከተላችሁ የተነሣ በሰዎች የተናቃችሁና ስፍራ የማይሰጣችሁ ከሆነ፣ በጌታ ደስ ይበላችሁ። ምክንያቱም በጌታ የከበራችሁ በሰይጣን ደግሞ የተፈራችሁ ናችሁና። አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ። አማኝ ከመሆኑ የተነሣ በመሥሪያ ቤቱ ስፍራ የማይሰጠው፣ ከጨለማው ሥራ ጋር ባለመተባበሩ ጓደኞቹ የሚያገሉት፣ ነገር ግን በእግዚአብሔርና በሥራው ዘንድ ታማኝ የሆነ አንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚሠራ ሰው ነበረ። ሁልጊዜ በሰዎች ዘንድ የከበሬታ ቦታ አልነበረውም፣ በጌታ ዘንድ ግን ነበረው፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር ይህን ባሪያውን አሰበ። ስሙንም ድንገት በሥራ ገበታው ላይ እያለ ይጥለዋል፣ አረፋም ይደፍቃል። የሥራ ባልደረቦቹ ተደናግጠው ይሸከሙና እየተሯሯጡ ወደ ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ይዘውት ይመጣሉ። ሥራ አስኪያጁም ተደናግጠው ከመቀመጫቸው እየተነሡ፣ "ምንድን ነው? ምንድን ነው? ወደ እኔ ይዛችሁ የምትመጡት" ይሏቸዋል። ሰዎቹም፣ "ይህን ሰው አጋንንት ጥሎት ነው፤ አንድ መላ ይበሉ" ይሏቸዋል። ሥራ አስኪያጁም እየተርበተበቱና የሰውየው አጋንንት ወደ እርሳቸው የሚዛመት እየመሰላቸው ቀጭን ትእዛዝ ሰጡ። "ይህንን ሰው እዛ መጋዘኑ ጋ ወዳለው ጴንጤ ይዛችሁ ሂዱ። እርሱ ጋ ነው ለዚህ ችግር መፍትሔና መድኃኒት ያለው እንጂ፣ እኔ ጋ ምንም የለም" ብለው መለሱ። ሰውየውንም እዛ ወሰዱትና አማኙ ጸልዮለት ተፈወሰ። እናንተ ጋ መፍትሔ አለና በጌታ ደስ ይበላችሁ። እናንተ ጋ ለበሽተኞች መድኃኒት፣ ለተራቡት ጥጋብ፣ ለተጠሙት እርካታ አለና በጌታ ደስ ይበላችሁ። ዛሬ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና እንደ ቃሉ በመሄዳችሁ ምክንያት በሰዎች የተናቃችሁ፣ ስፍራ የሌላችሁ ትሆኑ ይሆን? የምስራች በእግዚአብሔር ዘንድ የከበራችሁ ናችሁና ደስ ይበላችሁ።» መምህሩ የህንን ካሉ በኋላ ትምህርታቸውን ማስተማር ቀጠሉ።

አዎ፣ ወገኔ ሆይ፣ ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ትገኝ ይሆን? ከላይ እንደተጠቀሰው አማኝ በሰዎች የተናቅህ ሆነህ ቢሆን፤ በጌታ የከበርህ ነህና ደስ ይበልህ! በሰዎች ስፍራ የሌለህ ቢሆን፣ በጌታ ስፍራ አለህና ደስ ይበልህ! ክርስቶስ ከሌላቸው የዓለም ታላላቆች የማይገኝ ታላቅ ነገር በእኛ አለና ደስ ይበለን። ይህንንም አስተውለን እንድናልፍ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም:- የልጅነት ሥልጣን ተሰጥቶሃልና፣
ተጠቀም በስሙ የክርስቶስ ባሪያ።

ሮሜ 8:28፤ 2ኛ ነገ. 6:16
ዘፍጥ. 39:9

# ጥቁር አባቡሴ

ሰባኪው በክፍላቸው ተራ ቆመው ስለ እምነት እንዲህ እያሉ ያስተምራሉ:-

«ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብ. 11:6):: በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ብዙ የምንታመንባቸው ነገሮች ይኖራሉ:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ውጭ ከሆኑ እርሱን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም:: አንዳንድ ሰዎች በሰይጣን ያምናሉ፤ ሌሎች በገንዘባቸው ይታመናሉ፤ ሌሎች ደግሞ በጠንቋይ፣ ሌሎች ደግሞ በሌላ በሌላ:: ይህ ሁሉ ለሕይወታችን ፋይዳ የለውም:: ሲጠሩት የሚሰማውንና የሚረዳውን፣ ከዘላለም ሥቃይና ሞት የሚያድነውን፣ በሰይጣንና በመንግሥቱ ላይ በድል ተጫምተን እንድንኖር በሚያደርገው በእግዚአብሔር ብቻ ታመኑ:: እርሱ ደግሞ ለታመኑበት ታማኝ ነው:: ማንንም አይንቅም::» ስብከታቸውን በትጋት ለሚሰማቸው ጉባኤ ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በሕፃናት የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ከጓደኞቹ ጋር እየተገኘ የሚማር አንድ ትንሽ ልጅ ነበረ:: ምንም እንኳን ቤተሰቦቹ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰይጣን እያደሩ ቢቃወሙትም፣ እርሱ ግን መማሩን ቀጠለ:: ታዲያ ገና ከልጅነቱ እግዚአብሔር ልቦናውንና አእምሮውን ከፍቶለታልና በመንፈሳዊነቱ እያደገ ሄደ:: ቤተሰቦቹ እንዳይጸልይ በቤት ስለከለከሉት በትልቁ ቁምሳጥን ውስጥ እየተደበቀ ቁምሳጥን ሳያግደው ለሚሰማው አባቱ መጸለይ ጀመረ:: አባቱ ለወትሯቸው ጠንቋይ ቤት መሄድ ይወዳሉ:: ነገር ግን ከዚህ ልጅ ጸሎት ወዲህ አጋንንቱ እንዳይሠራ ታግዷል:: እንደተለመደው አንድ ቀን ጠንቋይ ቤት ለማስጠንቀል ሄደው አባቱ በጠንቋይ አገልጋዩ በኩል ጥቁር አባቡሴ የሚለዩ ጊዜያዊ ስም ተሰጥቷቸው ወደ ጠንቋዩ መጋረጃ በተራቸው ተጠርተው በቀረቡ ጊዜ ጠንቋዩ በጩኸት ድምፅ፣ "ጥቁር አባቡሴ መጀመሪያ በቤትህ ያለውን እሳት አጥፍተህ ናና እፈውስሃለሁ::" አላቸው:: በዚህ ጊዜ ቤት ሄደው ሚስታቸውን እሳት ቢጠይቁ ከምድጃው እሳት በስተቀር ሌላ የለም:: እርሱኑ በሁለት እንስራ ውኃ ቸልሰው አጠፉና ሄዱ:: በዚህ መሃል ሚስት ቅዳሜ ጠዋት ገበያ ልትሄድ ገንዘብ ልታወጣ ቁምሳጥኑን ስትከፍት ማሙሽ ኩርትም ብሎ ይጸልያል:: ደነገጠችና፣ "ልጄ አንተ ነህ ለዚያ ጠንቋይ እሳት ሆነህ የምታስጨንቀው:: ነገሩ እንዲህማ ከሆነ ና ሳሉን ቤት

ጸልይ።" አለችው። አባትየውም ለጠንቋዩ ግፌት በቀረቡ ጊዜ፣ "ምንም እሳት የለም፤ እሉ። ጠንቋዩ ግን "ምንም እሳት የለም ትለኛለህ፤ አሁንማ እሳቱ ከቁምሳጥን ወጥቶ ቤቱን ሞልቶታል።" አለ። አባትየውም እየተናደዱ እቤት ሲመጡ የሆነውን ታሪክ ሁሉ ከባለቤታቸው ሰሙ። ከዚያም፣ "በልጃችን ውስጥ ያለው እሳት ኃይል ከጠንቋዩ የበለጠ ከሆነማ፣ እኛም በልጃችን አምላክ ከዛሬ ጀምሮ እንታመናለን።" አሉ።

አዎ፣ አምላካችን ለታመነበት በእውነት ለቆመ ሰው፣ እርሱ ማንንም አይንቅም፤ ይልቁንም ጠላትን አዋርዶ ልጆቹን ከፍ ከፍ ያደርጋል፣ ያጸናልም። በእንደዚህ ዓይነት ኃይል ጌታ ላይ ታምነንና ታውቀን የሰይጣንን መንግሥት እያስጨነቅን የእምነት ሩጫችንን በድል እንድንፈጽም እግዚአብሔር ራሱ ጸጋውን ያብዛልን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።» (ማር. 2:5)

ግጥምጥም፡- ለጠንቋዩ ጠንቋይ ለምን ትሆናለህ

መንግሥቱን የሚያፈርስ ሥልጣኑ ተሰጥቶህ።

ዕብ. 11:1
ዘኍል. 23:23

# ፈታኙን እምቢ በል

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም::» (ኤር. 29:11)

ሰባኪው: ፈታኙን እምቢ ስለማለት ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ፣ «መቼም በሕይወታችን የክፉ ክፉ ብለን የምንለው አሳቢና ተቆርቋሪ የመሰለ ጎጂ ጠላት ሲኖረን ነው:: ለእኛ ለክርስቲያኖችም አሳቢ የመሰለው ጎጂ ጠላታችን ሰይጣን ነው:: ሰይጣን ዛሬ ብዙ እኛን የማጥቂያ መንገዶች ዘርግቷል:: ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው አሳቢ መስሎ መቅረቡ ነው:: ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈተናውን ያቀረበው እንዲህ ብሎ ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እነዚህን ድንጋዮች ወደ እንጀራ ለውጠህ ብላ! (ማቴ. 4:3) እዚህ ጋ ሰይጣን አሳቢ፣ ተቆርቋሪና አዛኝ መስሎ ነው የቀረበው:: ዛሬም "የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሽ እንዴት እስካሁን አላገባሽም? ሰው በ18 ዓመቱ ያገባል፣ አንቺ ግን ይኸውና ሁለት አሥራ ስምንት ደፍነሻል:: ለምን ያንን ዓለማዊ ሰው አታገቢም:: ወደ ጌታ ታመጪዋለሽ፤ ብቻሽን ከመሆን ይሻልሻል፤ ይህንን ዓለም ብቻሽን አትገፊውም" ብሎ አሳቢ ሆኖ መርዙን በማር ቀብቶ ያመጣል:: ለአንዳንዱ ደግሞ፣ ለምን ጉቦ አትበላም:: ከአንተ በኋላ የተቀጠሩ ይኸው በዓመታቸው ፎቅና ምድር ቤት ሲሠሩ፣ አንተ ይኸው አሥር ዓመትህ እስካሁንም ለምድር ቤቱ ተቸግረህ ነው ያለኸው> ይለዋል:: በዚህ ሁሉ፣ "እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ አምላኬ ለእኔ በጽድቅና በትክክለኛው መንገድ የሚያዘጋጅልኝ ይሻለኛልና አልፈልግም::" ብላችሁ ፈታኙን ተቃወሙ::» ለዚህ ግሩምና መሠረታዊ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ:-

አንድ ወጣት ክርስቲያን በአንዲት ኮረዳ ላይ የሰፈረውን አጋንንት በጌታ ስምና ሥልጣን ለማስወጣት በማሰብ፣ «በኢየሱስ ስም ልቀቃት» እያለ መጸለይ ጀመረ:: ልጅቷ ሲያዩዋት በሥጋ በጣም ቆንጆ ልጅ ነበረችና ሰይጣን ይህንን ተጠቅሞ የዚህን ወጣት አእምሮ ለመለወጥ አሰበ:: ክርስቲያኑም ልጅ እየገሠጸ መጸለዩን ቀጠለ፤ «በኢየሱስ ስም ውጣ፣ በኢየሱስ ስም ውጣ::» እያለ መጸለዩን ቀጠለ:: በዚህ ጊዜ በልጅቷ ውስጥ ያለው አጋንንት እምቢ አልወጣም» አለ:: «ለምን?» ቢለው፣ «እኔን ውጣ ውጣ የምትለኝ፣ እኔ ከወጣሁ በኋላ አንተ

እርሷን ልታገባት ነው አይደል?» አለው:: በዚህ ጊዜ የሚጸልየው ወጣት ልጅ፣ «ሰይጣን እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ ሰው ያለሰበውን ታሳስባለህ» ብሎት አረፈው::

አዎ፣ ሰይጣን ክፉ ነው:: ሰው ያላሰበውን አሳቢ መስሎ ግብግ በማቅረብ ይፈትነናል እና ፈታኙን እምቢ እንበል:: ጌታችን ሰይጣን ያቀረበለትን ሦስት ፈተና ሦስት ለዜሮ በመሸኘት አሸንፎታልና እኛም የእርሱን ምሳሌ እንከተል እንጂ ሦስት እኩል መውጣት የለብንም:: እግዚአብሔር ስለ እኛ ያስባልና ፈታኙ የሚያስብልንን እምቢ እንበል::

ግጥምጥም:- ባፉ ማር ጠብ ይላል ውስጡ ግን እሬት ነው፣

ፈታኙን እምቢ በል መጨረሻው ሞት ነው::

ምሳሌ 16:8
ማቴ. 4:1-11

# ኑር ያልኩት ይኖራል!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።» (ዮሐ. 1:12)

ሰባኪው ለእግዚአብሔር ልጆች ስለ ተሰጠው የልጅነት ሥልጣን ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ:- «በዚህ የተሰበሰብን ሁላችን እግዚአብሔርን የተቀበልንና በስሙም ያመንን ከሆነ፣ የልጅነት ሥልጣን ተሰጥቶናል። ይህም ሥልጣን በሁለት ይከፈላል። አንደኛው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ቀድሞ የሰይጣን/የቁጣ/ ልጆች ነበርን፣ አሁን ግን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፤ የመንግሥቱም ወራሾች ነን። ሁለተኛው፣ በክፋው የመናፍስት ሥራ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶናል። በዚህ ዓለም ስንኖር ይኸኛውን ሥልጣን ልንጠቀምበት መቻል አለብን። መንግሥተ ሰማይ ይህ ሥልጣን አይሠራምና። ሰይጣን ምንም ያህል ማስፈራራቱ ብዙና ትልቅ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን ከእግራችን ሥር እንድንቀጠቅጠው የልጅነት ሥልጣንን ሰጥቶናልና በእምነት ተነሥተን እንጠቀምበት።» ይህንንም መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ግልጽ ለማድረግ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

በአንድ ከተማ ውስጥ የሚኖር አንድ አስፈሪ ጠንቋይ ነበረ። እርሱም፣ «እኔ የበላይ ነኝ፣ ኑር ያልኩት ይኖራል። ሙት ያልኩት ይሞታልና። ለእኔ ተገዙ» እያለ ሕዝቡን በማስፈራራት ይገዛል። ታዲያ ወደዚያ ከተማ የልጅነት ሥልጣኑን ብቻ ይዞ አንድ ወንጌላዊ ገባና ወንጌልን መናገር ሲጀምር፣ ብዙ ሰዎች ከአጋንንት እሥራት እየተፈቱ ወደ ጌታ መምጣት ጀመሩ። ይህም ወሬ ለጠንቋዩ ደረሰው። «አንድ ልዩ ኃይል ያለው ሰው ወደዚህች ከተማ ገብቷል። የኢየሱስንም ስም ሲጠራ ሰይጣን ያለበት ሰው ይወድቃል፣ አጋንንቱም ይጮህና ይወጣል።» አሉት። ይህም ጠንቋይ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወንጌላዊው በሄደበት ላለመሄድ ወሰነና ሲሸሽ ቆየ። ነገር ግን አንድ ቀን ቤተሰቡን ጠራና፣ «በተከበርኩበት አገር እስከ መቼ እየሸሸሁ እኖራለሁ። ሂዱና ወንጌላዊውን ጥሩትና ይለይልን። ግን መጀመሪያ ምናልባት ሰይጣን ይዞኝ ከወደቅሁ እንዳልጎዳ ጆባ አንጥፉልኝ» ብሎ አዘዘና ወንጌላዊው ተጠራ። ወንጌላዊውም ገና ከቤቱ በራፍ ሲደርስ ጠንቋዩ ጮኸና በታላቅ ድምፅ እንደፈራው ጆባው ላይ ተዘረጋ። በዚህ ጊዜም ወንጌላዊው በተሰጠው የልጅነት ሥልጣን ተጠቅሞ በኢየሱስ ስም በመጸለይ ከሰይጣን እስራት የከተማዋን ጠንቋይ ነፃ አወጣው።

አዎ፣ በእኛ ላይ ያለው በእነርሱ ላይ ካለው ይበልጣልና፣ የተሰጠንን የልጅነት ሥልጣን በክፋው ሥራ ላይ እንጠቀምበት። ወደ እውነተኛውም ብርሃን እንዳይመጡ የሰዎችን አእምሮ ያሳወረውን ሰይጣንን በኢየሱስ ስም አስወግደን፣ ሰዎችን ለክርስቶስ እንድንማርክ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ጥቅስ:- «አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ፣»

ግጥምጥም:- በሥልጣን ላይ ሥልጣን ተሰጥቶኛልና፣
በአምላኬም ስም ልዝመት ዛሬም እንደገና።

የሐዋ. 16:16-18

# «በሕግ አምላክ!»

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ...» (ያዕቆብ 4:7)::

ሰባኪው፣ «በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች አንዳንድ እንደ ቃሉ ያልሆኑትን ነገሮቻችንን ማስተካከል ስላለብን በእነርሱ ላይ ትምህርት እሰጣለሁ:: ይኸውም ለምሳሌ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ በምንሰበሰብበት ጊዜ ሰይጣንም አብሮን ተቀምጦ ወይም አዚምን ረጭቶ ምንም ሳይሆን ይወጣል:: የእግዚአብሔር ቃል የሚለው፣ <እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል> ነው:: ይህ የቃሉ እውነት በእኛ የማይፈጸመው ታዲያ ለምንድን ነው? ለእግዚአብሔር በሙሉ ኀይላችን ከመገዛት ይልቅ ዐመፀኞች ስለሆንን ነው:: ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ፈንታ በኃጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለ ራቅን ነው:: ከእግዚአብሔር ደግሞ ከራቅን ሰይጣን ወደ እኛ ይቀርባልና ከእግዚአብሔር እንራቅ:: ለእግዚአብሔር ካልተገዛን ሰይጣን ለእኛ አይገዛምና ለእግዚአብሔር እንገዛ» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

«በአጋንንት ኀይል ቤተሰቡንና አካባቢውን ስላወከ በሰንሰለት ቤቱ ከታሰረ ሰንበት ብሏል:: እዚያው ሰፈር የሚኖር አንድ አማኝ አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያኑ የተካሄደውን ኮንፈረንስ ተካፍሎ በተነቃቃ መንፈስ መጣና በሰይጣን ወደ ተያዘው ሰው ቤት ሄዶ፣ "ዛሬ እጸልይለታለሁና ወደ ታሠረበት ክፍል አስገቡኝ" አለ:: ቤተሰቦቹም፣ "ተው እባክህ ብዙ ሰዎች መጥተው ጸልየው አልወጣምና ላንተም ሊወጣ አይችልም፣ ይቅርብህ" ቢሉት እንቢ አለ:: ወደ ክፍሉም ገባ:: "ሰንሰለቱን ፍቱትና ሁሉም ሰው ይውጣ" አለ:: ሁሉም ሰው ወጣ:: አጋንንቱም የሰፈረበት ወጣት ፈርጠም ያለ ነበርና ማጅራቱን ያዘና እግሩ ሥር አስገብቶ ሁለት ጊዜ በክርኑ ሲነርተው "ኡ ኡ" ብሎ አንቧረቀ:: ሰዎቹ ገቡ፣ ሦስተኛ ሊደግመው ሲል <በሕግ አምላክ!> ብሎ ጮኸ::»

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ፣ ሰዎችን ከሰይጣን እስራት ነፃ የምናወጣው ለእግዚአብሔር በመገዛትና ወደ እርሱ በመቅረብ እንጂ፣ ይህንን ሳናደርግ በኮንፈረንስ ተነቃቅተን በመምጣት ብቻ አይደለም:: ዛሬ አማኞች ሁላችን እግዚአብሔርን በመፍራትና የቅድስና ኑሮ በመኖር ብንመላለስ ከፊታችን ምንም ኃይል አይቆምም:: የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኀይል ታደርጋለችና::» ለእግዚአብሔር የማይታዘዙትን ለመገዛት፣ ከእግዚአብሔር የራቁትን ለማቅረብ ዛሬ ዲያብሎስ እያገሳ በዙሪያችን ይዞራል:: ሰይጣን መንፈስ ነው:: መንፈስን መምታት (መቃወም) የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነውና ሥጋዊነታችንን ትተን በጌታ መንፈስ የተሞላን እንድንሆን ጌታ ይርዳን:: አሜን!

ግጥምጥም:- ሰይጣን ሕግ የለውም በሕግ አምላክ አትበል፣
ወደ አምላክ ቀርበህ መንፈሱን ተቀበል::

1ኛ ጴጥ. 5:8፣ 9
ዮሐ. 9:31

# የመቃብር አፈር

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም::» (ሮሜ 10:11)

ሰባኪው: «በሰማይም ሆነ በምድር ለማዳንም ሆነ ለመግደል ሙሉ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሥጋንም ነፍስንም ሊያድን ወይም ሊያጠፋ የሚችል ባለሥልጣን ጌታ ብቻ ነው:: ይህንን ካለመረዳት ዛሬ ሰዎች ለነፍሳቸውም ሆነ ለሥጋቸው ፈውስንና ደስታን ፍለጋ ከእግዚአብሔር ውጪ ሲጓዙ ይታያሉ:: አንዳንዱ ለጠንቋይ፣ አንዳንዱ ለአድባር፣ ሌላውም ለዛፍ ሲያጥንና ሲሰግድ ይታያል:: ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድና እጅ የሌለበት መንገድ ነውና ተመለሱ:: ከድህነት የሚያወጣ ጌታ እንጂ ሰባኪ አይደለም:: ከጭንቀት የሚያሳርፍ ጌታ እንጂ መናፍስት ጠሪ አይደለም:: ከኃጢአት የሚያድን ጌታ እንጂ የእኛ ሥራ አይደለም:: ከሞት የሚያድን ጌታ ኢየሱስ እንጂ ጠንቋይ አይደለም::» ለሚለው መሠረታዊ የክርስትና ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ:-

ክፍለ ሀገር ለአገልግሎት ሄጄ የተቀበለኝ ወንጌላዊ ቤት ሄጄ ሁለት እኅቶችን አስተዋወቁኝ:: «ይህችኛዋ ባለቤቴ ነች:: ይህችኛዋ ደግሞ ጌታ የሰጠኝ እኅቴ ናት» አለኝ:: «ጌታ የሰጠኝ እኅቴ ስትል ምን ማለትህ ነው ስለው፣ ታሪኩን አጫውትሃለሁ ብሎ ጥቂት ካረፍኩ በኋላ ያጫወተኝን ልንገራችሁ:: ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ከእኅቱ ጋር አብረው እየኖሩ ሳለ እርሷ በጠና ትታመማለች:: እርሷን ለማዳን ያልሄደበት የለም፣ መፍትሔ ግን ጠፋ:: አልጋዋ ላይ ተኝታ እስከማትታይ ደረሰች:: በመጨረሻም ላይ የሄደበት ጠንቋይ ወደ ጌታ እንዲመጣ ምክንያት የሚሆነውን ነገር ሳያውቅ አዘዘው:: «እኅትህ የምትድነው ለሦስት ቀን ገጣባ አህያ ላይ እያስቀመጥክ፣ ለሰባት ቀን የመቃብር አፈር ጠዋት ጠዋት እያጠጣህ፣ የጅብ ቆዳ አንገቷ ላይ ስታስርላት ነው::» አለው:: እኅቱን ለማዳን የታዘዘውን አደረገ:: እርሷ ግን ለውጥ አላመጣችም:: አንድ ቀን ተስፋ ቆርጦ እንቅልፍ አጥቶ ፍጥጥ ብሎ አደረ:: በሰፈራቸው መሃል ካለው ጸሎት ቤት ፕሮግራም መሪው የሚናገረው አንዳንድ ቃላት በድምፅ ማጉያው እያመለጠ ጆሮው ይገባል:: ከዚህም ውስጥ እንዲህ የሚለውን ሰማ:- «ማዳን የእግዚአብሔር ነው!» ብድግ አለ:: አዎ፣ ማዳን የጠንቋይ ሳይሆን

የእግዚአብሔር ነውና እነዚህ ጴንጤዎች ጋር ሄጄ ልሞክር ብሎ እኅቱን ተሸክሞ አመጣት ። በእርግጥም ማዳን የእርሱ የሆነ ባለሥልጣን ጌታ እኅቱን ፈወሳት። ዛሬ እርሱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንጌላዊ፣ እርሷ ደግሞ በመዘምራን ቡድን ውስጥ ገብታ አምላኳን ታገለግላለች። ያለ አባትና እናት ያሳደጋቸውን ጌታ ሥራ ሲናገር እንባ በጉንጮቹ ይወርድ ነበር።

አዎ፣ ወገኖች፣ በእርግጥም ማዳን የእግዚአብሔር ነው። ነፍሳችንንም ሥጋችንንም ከጊዜው ጥፋትና ከገሃነም እሳት ሊያድን የሚችል እግዚአብሔር ነውና በእርሱ ላይ ብቻ እንታመን። እግዚአብሔር አንድምታ የሌለው ብቸኛ አዳኝ ነው። በዚህ ምድር መቶ እጥፍ ማኖር በላይ የዘላለም ሕይወትን መስጠት የሚችል በቀራኒዮ መስቀል ደሙን ያፈሰሰው ክርስቶስ ብቻ ነውና ከዛሬ ጀምሮ ሙሉ ሕይወታችንን ለእርሱ ሰጥተን ከዘላለም ሞት እንድናመልጥ ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- ሊገድልና ሊያድን ሙሉ ሥልጣን ያለው፣

ሊረዳህ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

| |
|---|
| ሮሜ 10:9 |
| የሐዋ.ሥራ 4:12 |

# ድንግል ማርያም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ:: ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና::» (ማቴ. 11:28-30)

ሰባኪው፣ «በዚህ ዓለም የምንኖር ብዙ የሚከብዱ ሸክሞች ያለብን ሰዎች ነን:: ከሁሉም ከሁሉም በጣም የሚከብደው ሸክም ደግሞ የኃጢአት ሸክም ነው:: እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፣ ይህንን የኃጢአት ሸክም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንድናራግፈው አደረገልን:: ቃሉ እንደሚል ከኃጢአት ሸክም ወጥተን ከገሃነም እሳት የምንድነው ከድንግል ማርያም የተወለደውን ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስናምን ብቻ ነው:: ከእርሱ ሌላ አዳኝ በሰማይም ሆነ በምድር የለምና፣ በእርሱ እመኑ፤ ከዘላለም ሞትም ትድናላችሁ፤ የከበደው ሸክማችሁም ይቃለላል:: ለነፍሳችሁም እረፍት፣ ለሥጋችሁም ፈውስ ታገኛላችሁ::» ለሚለው የአምላካዊ ቃል ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ:-

አንድ ሰው በቤቱ ሊደግሰው ስላለው ትልቅ ድግስ የሚያስፈልገውን የገብስ እህል ሸምቶ ለድግሱ እየተዘጋጀ እያለ የሸመተው የገብስ እህል መጠጡን በሙሉ መሸፈን እንደማይችል ተረድቶ እየተጨነቀ ሳለ፣ ይህንን ጭንቀቱን በቅርቡ ሊያቃልል የሚችል ሁኔታ ተፈጠረለት:: ይኸውም በሰፈሩ ውስጥ የሚሸጥ ገብስ ተሸክሞ፣ «ገብስ፣ ገብስ፣ ገብስ» እያለ የሚጮኽ ሰውን ሰማ:: ወጥቶም ወደ ቤቱ ጠራውና የተሸከመውን ገብሱን በሙሉ መግዛት እንደሚፈልግ ገለጸለት:: ገብስ ሻጩም፣ «እግዚአብሔር ረዳኝ፣ ከመሸከምና ከመዞርም አሳረፈኝ» ብሎ እሺ እንደማለት በተቃራኒው እንዲህ ሲል መለሰለት»፣ «ጌታዬ፣ ሁሉንም ገብስማ አልሸጥልዎትም:: ምክንያቱም ሁሉንም ገብስ ለእርስዎ ሸጬ እኔ ምን ተሸክሜ ልዞር ነው::»

አዎ፣ በእኛም በሰው ልጆች ሕይወት ይህ ዓይነት ሁኔታ ይታያል:: እግዚአብሔር፣ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑና እረፉ» ሲል፣ የየራሳችንን ምክንያት በመስጠት እንቢ ሸክሜን እራሴ እሸከማለሁ እንላለን:: ምናልባት ብሎልን ወደ ጌታ ከመጣንም ሁሉንም ሳይሆን ግማሹን ሸክም ለእኛ እናስቀራለን:: ዛሬ ጌታ እንዲህ ይላል፣ «ሙሉ ለሙሉ በእኔ ብቻ በማመን ሁሉንም ሸክማችሁን በእኔ ላይ ጣሉና እረፉ::» ቃሉን ሰምተን እንድንታዘዝ አምላክ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ሸክሜን ለሚሸከም ለጌታ ሰጥቼ፣
ቀና ብዬ ሄድኩኝ ከእሥር ተፈትቼ::

| |
|---|
| ዮሐ. 10:9 |
| የሐዋ. 3:6-9 |

## *ክፍል 6*
## *እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕይወትና አገልግሎት*

# ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ!

***የቃል ጥናት ጥቅስ: - «በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» (ሮሜ 12:13)***

ሰባኪው፣ «ለእግዚአብሔርም ሆነ ለእኛ ትልቁ ቁም ነገር በእርሱ ፊት ከልባችን ተለውጠን እርሱን መከተላችንና ማምለካችን እንጂ ብዙ ዓመት ያለ ለውጥ በቤቱ መቆየታችን አይደለም። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብጥብጥ፣ መከፋፈል፣ መገፋፋትና መቆሳሰል ያለው ለምንድን ነው? ብንል ያልተለወጥን ሰዎች ስለሆንን ነው። 'ልጄ ሆይ፣ ልብህን ስጠኝ' ላለው ጌታ ልባችንን ስላልሰጠን ነው። ምን አልባት ልንሰብክ፣ ልንዘምር፣ የተለያዩ አገልግሎቶች በቤቱ ልንሰጥ እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችንን ሲመለከተው ከልቡ ጋር ካልሆነ 'እንደ ልቡ ነው' ነው የሚለን እንጂ 'እንደ ልቤ ነው' አይልምና እንመለስ። አንዳንድ ጊዜ ነገራችን የተገላቢጦሽ ይሆናል። ይኸውም ልባችንን ሰጥተንና ተለውጠን መከተልና ማገልገል ሲገባን ልባችንን ራሳችን ይዘን የልባችንን ለምን ጌታ አላደረገልንም ብለን እናኩርፋለን፤ 'ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ' እንደተባለው እንሆናለን። ስለዚህ ትልቁ ነገር ከልብ ተለውጠን ጌታን መከተላችን ዓለምን መናቃችን ነው እንጂ ብዙ ዘመን በእግዚአብሔር ቤት ያለ ለውጥ መቆየታችን አይደለምና ዛሬውኑ እንለወጥ።» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ እንደዚህ ሲሉ ተናገሩ።

በአንድ የጨዋታ ሜዳ ላይ የሰርከስ ጨዋታ ይካሄድ ነበር። ሲያዩት የሚያስፈራራ ዓይነት ጭምብል /ማስክ/ ሰውነታቸውን ሙሉ ለብሰው ትልቅ ክንፍ ዓይነት በጉናቸው አድርገው በመድረኩ ላይ ከወዲያ ወዲህ እየሮጡ በአስገራሚ ሁኔታ እየተገለባበጡ ያሳያሉ። ትርኢቱ ሳያልቅ ድንገት በረዶ የቀላቀለ ኃይለኛ ዝናብ ይመጣና ጨዋታውን ያቋርጠዋል። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ለመጠለል በየፊናው ይበተናል። ሰርከስ ለማሳየት አስፈሪ ልብስ ከለበሰው ሰው አንዱ ለመጠለል ወደ መንደር ሲሮጥ ቀኑ ሰንበት ነበርና ሰዎች እያመለኩ ያሉበት ቤተ ክርስቲያን እየሮጠ ዘው ብሎ ይገባል። እዚያም ያሉት ሰዎች ምን መጣብን በማለት በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ በመውጣት ይሸሻሉ። በዚህ ጊዜ ለማምለጥ አቅም አጥተው ወደ ቆሙት አንዲት አሮጊት ሴት ይህ

የሰርከስ ሰው ጠጋ ብሎ ለምን ሰው እንደሚሸሽ ሊጠይቃቸው ቃል ከማውጣቱ በፊት አሮጊቷ ቀደም አሉና፣ «ሰይጣን ሆይ፣ አርባ ዓመት ሙሉ በቤተ ክርስቲያን ልሁን እንጂ አንተን ነበር ስከተል የኖርኩት» ብለውት አረፉ።

እዎ፣ ወገኖች፣ በልባችን ተለውጠን ጌታን እናገልግል፤ እናምልክ እንጂ ዘመን እየቆጠርን ከርሞ ጥጃ መሆን አይገባንምና ራሳችንን እናስተካክል። ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምረው ፍርድ እንዳያገኘን ጌታ አብዝቶ ይርዳን። አሜን።

*ግጥምጥም:- የልቤን ደብቄ አፋዊ ከምሆን፣* | *ያዕ. 1:8፣ 26*

*ልቤን አስረክቤ እንደ ልቡ ልሁን።*

# ገንፎ በቂቤ

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «አባቶች ሆይ፣ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው።» ቆላ. 3:21*

አንዲት ሚስት ከልጆቿ ለይታ ለባለቤቷ ጥሩ ምግብ /ገንፎ በቅቤ/ አዘጋጀች። ይህንን ምግብ በጓዳ ጨለማ ስፍራ ውስጥ ባልዬው ሲበላ አንዱ ትንሹ ልጅ ከልጆቹ ሁሉ ጋር ለከብት ጥበቃ ሜዳ ሳይሄድ ቤት ቀርቶ ነበርና በቂቤ የተዘጋጀው የገንፎ ሽታ አወደው። ወደ ጓዳው አባቱ እንዳለ ያውቅ ነበርና አባቱን ጠርቶ መጠየቅ ጀመረ። «አባዬ» አለው፣ «አቤት» አለ አባት። «ምን እየበላህ ነው?» አለው እርሱ ጠዋት ከወንድሞቹ ጋር እንደ ነገሩ ስለ ተሸኘ በመቆጨት። አባትም፣ «አፈር እየበላሁ ነው» አለው። ልጅም አፈር እንዳልሆነ በሽታው ስላወቀና የእናቱም እንዲህ ዓይነት መሠሪነት ስላናደደው ድምፁን ከፍ አድርጐ፣ «አባዬ፣ አፈር ከሆነ የምትበላው እኔም መጥቼ ልብላ» አለው። አባትየውም የልጁ ተከታታይ ጥያቄ ገንፎውን እንዳይበላ እያወከው ስለሆነ ተናዶ ለልጁ እንዲህ አለው። «ልጄ፣ አፈር ለመብላት ትፈልጋለህ?» አለው። «አዎን» አለ ልጁ። «ጥሩ አፈር ለመብላት ከፈለግክ እዚያው ያለህበት ጀምር። አፈር ሁሉም ቦታ አለና ከግድግዳው ጀምር» አለውና አረፈው።

አዎ፣ እውነተኛ ፍቅር ከራሱ ይልቅ ሌላውን ያስበልጣል፣ የሌላውን ጥቅም ያስቀድማል። ዛሬ በየቤታችን ለልጆቻችን ያለን ፍቅር ምን ያህል ይሆን? ይህ ከላይ ያለው አባት ልጁን አፈር ብላ ነው የሚለው። እኛስ? እናቱም የጐላ አድልዎ እያሳየች ነው። እርስዎስ? የይስሐቅ ቤት የተበተነው በአድልዎ ነው። የእርስዎስ ቤት ምን ዓይነት ይሆን? ምን ዓይነት ዜጎች እያፈራን ይሆን? እግዚአብሔር የሰጠንን ሲሳይ ያለ ከንቱ ወዳሴ በፍቅርና በእውነት አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለን ተካፍለን እንድንኖር የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

ዘፍጥ. 27:1-46
ፊልጵ. 2:3-4

ግጥምጥም:- *ሁሉም ይደርሳል ፅዋው ሲሞላ፣*

ከአፈር በላይ ሆኖ ለምን አፈር ይብላ።

# ጴንጤው ቦክሰኛ

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «ስለ ራሴ ግን ከድካሜ በቀር የምመካበት ነገር የለኝም» (2ኛ ቆሮ. 12:5)።

መጋቢው መልእክታቸውን ለመስማት ለተሰበሰበው ሕዝብ እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ። «በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች ሁሉ የምንመካበት ብዙ ነገሮች አሉን። ለመሆኑ የእነዚህ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ማን እንደሆነ አውቃችኋል? እግዚአብሔር ነው። ስለሆነም ትምክህታችን እርሱ ብቻ ሊሆን ይገባል። ዛሬ እውነቱን ልንገራችሁ፣ ሊመኩበት በሚያስመካው በዘላለሙ ጌታ ላይ ብቻ ትምክህታችንን ካላደረግን ከስረናል። ምናልባት በባንክ ባላችሁ ገንዘብ ብትመኩ ነገ ስለሚረግፍ ወይም ስለሚጠፋ ትምክህታችሁ ከንቱ ነው። ምናልባት በጊዜው ብትመኩ፣ ጊዜው ያልፋልና ከንቱ ነው። ወይም በጉልበታችሁ ብትመኩ፣ ጉልበት የእግዚአብሔር ነውና ከንቱዎች ናችሁ። እንግዲህ ትምክህታችን ምንድን ነው? ትምክህታችን ዛሬ ሲያምኑት ነገ በማይከዳና በማይለወጠው፣ ነገር ግን በሚለውጠው በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል።» ለዚህም ዘላለማዊ እውነትነት ላለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ። ለዚህም

ሰፈሩ ሁሉ የሚፈራው አንድ ሰውነቱ የፈረጠመ ቦክሰኛ ነበረ። ማንም እርሱን ቀና ብሎ አያይም (ዝንቡን የሚያባርር የለም)። አለበለዚያ ቀና ብዬ አያለሁ እናገራለሁ ቢል ጡንቻው ከምድር ጋር ነው የሚደባልቀው። በእንዲህ ሁኔታ ሲኖር ሳለ ከፍ ካለው በላይ ከፍ ያለው እግዚአብሔር በመለኮታዊው ኃይሉ የዚህን ቦክሰኛ ልብ ሰበረና ጌታን ተቀበለ። አማኝ መሆኑን የሰፈሩ ሰዎች ሁሉ ሰሙ። እሰይ እኛም አረፍን አሁን አይመታንም ብለው ተደሰቱ፤ የድሮ ፍርሃታቸውንም አስወግደው በፊቱ በንቀት መመላለስ ጀመሩ። ትንሽ ትልቁ፣ «ጴንጤው ቦክሰኛ» እያለ ማሾፍ ቀጠለ። አንድ ቀን ጴንጤው ቦክሰኛ ተበሳጨ፣ የድሮው ነገር ትዝ አለው። አንድ ልጅ እንደተለመደው፣ «ጴንጤው ቦክሰኛ» ብሎት ሲያልፍ ያዘና በቦክስ ሁለት ጊዜ ሲነርተው አማኞች በአካባቢው ደረሱና ገላገሉት። «ተው፣ ለምን ትማታለህ? አማኝ አይማታም» ቢሉት፣ «አይ፣ ጌታ ወንድ ልጅ እንዳለው ላሳያቸው ብዬ ነው» ብሎ መለሰላቸው።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ፣ የጌታ ልጅ መሆናችንን በሥጋችን ኃይል ማሳየት አንችልም፤ አልተፈቀደልንም። በፍቅር እና በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በከንቱ እየተነሣን እንድንመካ የሚያደርገንን የአሮጌውን ሰው ባሕርይ እናስወግድ፤ ጌታንም ክርስቶስን ለብሰን በብዙ ትሕትናና አክብሮት እንድንከተለው ራሱ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም፡- «በኃይልህ አትመካ ድንገት ይከዳሃል፣
በእግዚአብሔር ተመካ እርሱ ያዋጣሃል።

| |
|---|
| 2ኛ ቆሮ. 10:17 |
| ገላ. 6:14 |

# ሰላቢ የሰለበው ሀብት

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ቅንዓት እንደ ሲዖል የጨከነች ናት፤ ፍንጣሪዋም እንደ እሳት ፍንጣሪ ነው።» (ምሳ. 8:6)

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር ከሕይወታችን እንድናስወግደውና እንድንተወው የሚፈልገው ነገር በዚህ ዘመን ወገኖቼ ቅንዓትንና ምቀኝነትን ነው። ክርስቲያን በክርስቲያን ላይ መቅናት አይገባውም። የሌላው ማደግ የራሱም ማደግ እንደሆነ አድርጎ ሊቆጥር ይገባዋል። ጎረቤት በጎረቤት ላይ መቅናት የእርሱን ሀብት በሰላቢና በጥንቆላ ለማግኘት መፈለግ ኃጢአት ነው። ደግሞ ሰላቢ የሰለበው ሀብት ያጠፋል ወይም ይጠፋልና በጽድቅ የሚገኘውን ሀብት ተመኙ ። የእግዚአብሔር ቃል በሮሜ 13:13 ላይ መመላለሳችን በቅንዓት አይሁን ይላልና። ቅንዓትና ምቀኝነት የሥጋ ሥራ ናቸው። የሥጋ ሥራን የሚያደርጉ ደግሞ መንፈሳውያን አይደሉምና እንመለስ። ሰው በባልንጀራው ሕይወት መሳካት የሚቀናው ፍጹም ፍቅር ስለሌለው ነው። ፍቅር አይቀናምና (1ኛ ቆሮ. 13:4)። ቅንዓት ደግሞ እንደ ሲዖል የጨከነ ነውና ለመግደል እንኳ አይመለስምና ተጠንቀቁ።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ ቤተሰብ የመጀመሪያ ልጃቸው ሦስት ዓመት ከሆናት በኋላ እንደ ጌታ ፈቃድ ሌላ ልጅ ለመጨመር ወሰኑና ሚስት አረገዘች። የመውለጃዋም ጊዜ ከመድረሱ በፊት አዲስ ልጅ ስትመጣ የመጀመሪያዋ እንዳትቀና በተቻለ መጠን አእምሮዋን ለማዘጋጀት ሞከሩ። ልጅቱም ከእርሷ ያነሰ የሚያጫውታት ሕፃን ልጅ እስኪመጣ ቸኮለች። እናቲቱም በእግዚአብሔር በተመደበው ጊዜ ወለደችና ወደ ቤት መጣች። በዚህ ጊዜ ይህች ትልቋ ልጅ ለተወለደችው ሕፃን ልጅ ሁሉን እንደምትሰጥ ተናገረች። የእኔን ጡት ትጥባ፣ የእኔን ጡጦ ትጠጣ፣ በአልጋዬም ትተኛ አለች። ነገሩም ሆነ። ከሦስት ቀን በኋላ ግን ቅንዓት የሚባለው የውስጥ ቅንቅን ያዛት ልጅቷን ስታያት አልጋዋን ከመልቀቅ ይልቅ እየቀጠለች ሄደች። በዚህ ጊዜ ትልቋ የ3 ዓመቷ ልጅ ወደ አባቷ ጠጋ ብላ፣ «አባዬ፣ ይህችን ልጅ ከአልጋዬ ላይ ታነሣ ከሆነ አንሣ አለበለዚያ ጨፍልቄ ነው የምገልልህ።» ብላ ተናገረች።

አዎ፣ ወገኖቼ፣ ቅንዓት እስከ ሞት ያደርሳል። ሰው አይመርጥም እንደ ሲዖል የጨከነ ነውና እንመለስ። ዛሬ ወንድማችንን ወይም እኅታችንን ገፍተን ወይም አስወግደን የእነርሱን ቦታ በዐመፅ ለመያዝ አስበን ይሆን። እነሆ፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ «አይሳካልህምና ተመለስ። በቀል የእኔ ነውና አይከናወንልህም» ይለናል። አዎ፣ ለዚህ የእግዚአብሔር መልእክት ታዘን በእግዚአብሔር ፈቃድ እንድንኖር ጌታ ይርዳን። አሜን።

ዘኁል. 12:1-5
ምሳ. 6:34

ግጥምጥም:- በቅንዓት ወስደህ የወንድምህን ሀብት፣
እኔ እፈራለሁኝ ሳትበላው እንዳትሞት።

# እግዚአብሔር አይዘበትበትም

ሰባኪው፣ «ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል። በዚህ ምድር ላይ ስንኖር የእግዚአብሔርን ቃልና የእግዚአብሔርን መልእክት ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎች ፈውስና ጥቅም ማዋል አለብን እንጂ ለራሳችን ክብርና ጥቅም ማዋል የለብንም። ቃሉ ያላለውን በግድ ማስባል፣ እግዚአብሔር ያልገለጠውን በውሸት ተገለጠልኝ ማለት የሚያስነውር ብቻ ሳይሆን ወደ ገሃነምም ያስገባልና እንጠንቀቅ። በተለይም እኛ ሕዝቡን እንድንመራና እንድናስተምር እግዚአብሔር ያስቀመጠን ሰዎች እንደ ፈቃዱ እንጂ እንደ ፈቃዳችን እናድርግ፣ ለክብሩ እንጂ ለክብራችን አንድከም። ዛሬ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያንና በአገራችን መካከል መከፋፈል ለምን መጣ ብንል እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለማንኖር ነው፣ ቃሉን ወደ ጎን ትተን የእኛን አጀንዳ ስለአስቀደምን ነው፤ በሌላው ሥቃይና ድካም ላይ ተረማምደን የራሳችንን እንጀራ ለማደለብ ስለሞከርን ነው። እንመለስ። እግዚአብሔር አይዘበትበትም የሚባላ እሳት ነውና።» በሚለው ጠንካራና አስፈሪ መልእክታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

ከሁለቱ ወንጌላውያን አንደኛው ወደ ክፍለ ሀገር ሄዶ እንዲያገለግል የሚወስነው የሽማግሌዎች ቦርድ ስብሰባ በቀጣዩ ቀዳሜ ከመካሄዱ በፊት <ምናልባት እኔን ሂድ ይሉኝ ይሆናል> ብሎ የሰጋው ወንጌላዊ ከስብሰባው በፊት የሽማግሌዎች ቦርድ ሰብሳቢ (ሊቀመንበር) ቤት ማታ ሄዶ ለእርስዎና ለቤተሰብዎ ለመጸለይ ጌታ ልኮኝ ነው የመጣሁት» አለ። ሰብሳቢውም 12 ልጆች ወልደው ነበርና እነዚህም ልጆች በጥሩ ሁኔታ ቦታ ቦታ እንዲይዙላቸው ከባለቤታቸው ጋር የሚጸልዩበት፣ ሌላም ልጅ ላለመውለድ ባለቤታቸው ማኅፀናቸውን ያስቋጠሩበት ሰሞን ነበርና፣ «ለቤተሰብዎ እጸልያለሁ» ሲላቸው ደስ አላቸው፣ ጸሎቱም ተጀመረ። ይህ ከበስተ ኋላ ድብቅ አጀንዳ ያለው ወንጌላዊ ታዲያ በጸሎቱ መሐል ተነሥቶ እግዚአብሔር ሳይለው እንዲህ አለ፤ «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚስትህን ማኅፀን አለምልሜአለሁ ይላል»።

ወገኖቼ፣ በሕይወታችን ሊመጣ ያለው ይምጣ፣ ሊሄድም ያለው ይሂድ እንጂ እግዚአብሔር ያላለንን አንበል። እግዚአብሔር ያለውን ብለን ሳንጨርስ ያላለውን ማለት ዓመፅ ነው፤ ኃጢአት ነው ያስቀስፋልም። የምላስን ሽንገላ፣ መሠሪነትንና ግብዝነትን ከሕይወታችን አስወግደን እውነትን በፍቅር እየገለጽን የምንኖር ታማኝ ባሪያዎች ያድርገን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም...» (ገላ. 6:7)

ግጥምጥም:- እውነትን በእውነት ለአንተ ተናግሬ፣

ይጨምራል እንጂ መች ይቀንስ ክብሬ።

# ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም

የቃል ጥናት ጥቅስ «... በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ::» (ሮሜ 12:2)

ሰባኪው: «የክርስትና ሕይወት የሚያምረው የተለወጠ ልብ አብሮ ሲኖረው ነው:: በአሁኑ ጊዜ በተግባር የማይገለጽ ሥጋዊነት የበዛበት ያልተለወጠ ክርስትና ይዘን ግን ክርስቲያን ነኝ እንላለን:: እግዚአብሔር ይቅር ይበለን:: ክርስትና ክርስቶስ ነው:: ክርስቶስ ደግሞ በልቡ ትሑት፣ አቅምና ጉልበት እያለው ክብሩን ለሌሎች የተወ ጌታ ነው:: የእርሱ ልጆች ከሆንን ከልባችን መለወጥ አለብን እንጂ አፋዊ ክርስትና አያዋጣም:: በእግዚአብሔር ዘንድ ያልተለወጠ ሰው መሥዋዕቱ ተቀባይነት የለውም:: ስለዚህ በባህሪያችንና በተግባራችን ከዓለም ተለይተን እና ፈጽሞ ክርስቶስን በመምሰል ተለውጠን ልንከተለው ይገባል::» ለሚለው ግሩም የሆነ ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በከተማ አውቶቡስ ላይ ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ መናገር የሚወዱ አንድ ሰው አንድ ቀን የተለየ ነገር ገጠማቸው:: ሲመሰክሩ አጠገባቸው ሆኖ ይሰማ የነበረ አንድ ወጣት ልጅ እንዲህ እያለ ያሾፍባቸው ጀመር:: «ጴንጤው ሽማግሌ፣ ጴንጤው ሽማግሌ» ያልሰሙ መስለው ዝም አሉት:: አሁንም ማሾፉን ቀጠለ:: ቦታ ቀየሩ እየተከታተለ ለሰው ሁሉ እኚህ ጴንጤው ሽማግሌ ናቸው ይላል:: ታገሡት፣ አሁንም ደግመው ቦታ ቀየሩ:: እየተከተለ ያሾፍባቸዋል:: በመጨረሻም ላይ በጣም ስለተናደዱና ትዕግሥታቸው ስለአለቀ፣ «ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም» ብለው ሁለት ጊዜ በጥፊ አጮሉት:: ጠላትም ይህንን የሥጋ ሥራ ተጠቅሞ በአውቶብሱ ውስጥ ያለውን ሰው አስነሣባቸው: በልጁ ላይ ከሰነዘሩት ጥፊ ይልቅ በእርሳቸው ላይ የተሰነዘረው ድብደባ ስለበዛ ያለ መውረጃቸው ወርደው አመለጡ::

አዎ፣ ወገኖቼ፣ እኚህ ሰው ከተግባራቸው ሲታዩ ልባቸውም የተሰበረ አይደለም:: ልቡ የተሰበረ /የተለወጠ/ ሰው ሲሰድቡት ይመርቃል እንጂ አይረግምም፣ ወይም አይማታም:: የራሱንም ክብር ለማስከበር ኃይል አይጠቀምም:: ከዚህ ነገር ለመውጣት ጌታ ጥበብ እንዲሰጠው ይጸልያል እንጂ:: ስለዚህ የዚህን ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ አንከተል:: በግብዝነትም ሳንለወጥ አናገልግል:: ብዙ ቂምና ቁርሾ ይዘን በቤተ ክርስቲያን ግን በመድረክ ላይ እንደ መልአክ እንታያለን:: እግዚአብሔር አይዘበትበትም እርሱ የሚበላ እሳት ነውና ከእሳት ጋር መጫወቱን ትተን በፍርሃትና በተለወጠ ልብ እንድንመላለስ ሁሉን ችሎ የሚያስችለው አምላክ እራሱ በጸጋው ይደግፈን:: አሜን!

ግጥምጥም:- ላገልግለው እንጂ በተለወጠ ልብ ለእርሱ ሆኜ ትሑት ሮሜ 12:18
የአንጀት ክርስትና ለምን ይሁን የአንገት:: ሉቃስ 10:27

## የምድር ጨው ወይስ የእንግሊዝ ጨው?

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላለም ሞት ያዳነን እንድናመልከውና ለሌሎችም ብርሃንና ጨው እንድንሆን ነው እንጂ በመጥፎ የሕይወት ምስክርነት እየተመላለስን የወንጌል እንቅፋት እንድንሆን ፈጽሞ አይደለምና ዛሬ ሕይወታችንን ልንፈትሽ ይገባል:: እኛ ለጨለማው የምንገለጥ የዓለም ብርሃን እንጂ በጨለማው የምንዋጥ መሆን የለብንም:: በመልካም የሕይወት ምስክርነት ክርስቶስን የምናሳይ መራራውን የምናጣፍጥ የምድር ጨው እንጂ፣ ክርስትና እንደ እነርሱ ከሆነ በአፍንጫዬ ይውጣ የምንባል መራሮችና ለዚህ ዓለም የምንመች ሰዎች መሆን የለብንም:: ስለዚህም ዓለም ስታማ አብረን አንማ፣ ዓለም ስትቀና አብረን አንቅና፣ ዓለም ስትዘፍን አብረን አንዘፈን፣ ዓለም ስትሰርቅ አብረን አንስረቅ፣ ዓለም ስትጠጣ አብረን አንጠጣ፣ ዓለም ስትሰክር አብረን አንስከር፣ ዓለም ስታኮርፍ አብረን አናኩርፍ፣ ዓለም ስታምፅ አብረን አናምፅ:: የእግዚአብሔር ቃል፣ "ኖኅ በሥራው ዓለምን ኮነነ" (ዕብ. 11:7) እንደሚል የምድር ጨው ሆነን የዓለምን ክፉ ሥራ በጽድቅ በመለወጥ በሥራችን እንኰንን እንጂ በዓለም ሥራ አብረን እየተባበርን አብረን መኰነን የለብንም» ለሚለው ግሩምና አስደናቂ መልእክታቸው እንደሚከተለው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ወንጌላዊ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሲሰብክ የምድር ጨውን ከእንግሊዝ ጨው ጋር እያወዳደረ እንዲህ ተናገረ፣ «እኛ ክርስቲያኖች የምድር ጨው ነን እንጂ የእንግሊዝ ጨው አይደለንም:: እንደምታውቁት የእንግሊዝ ጨው ጊዜው ደርሶ ከሆዳችን እስከሚወገድ ጉትጉትጉት እያለ ያምሰናል:: ልክ እንደዚሁ በቤተ ክርስቲያን ያልተደረገውን ተደረገ፣ ያልታየውን ታየ እያሉ ወሬ በክርስቲያኖች መካከል የሚያመላልሱ፣ ቅዱሳንን የሚያጋጩና የሚያምሱ የእንግሊዝ ጨዎች አሉ:: እከሌ ከእከሊት ጋር እጮኛ ሆነ፤ እከሌ እኮ፣ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ሰርቆ ቤቱን ሠራ! እከሊት በተሳሳተ የዲቪ ባልና ሚስት ከአገር ልትወጣ ነው፤ እከሊት ከጋብቻ በፊት የወለደቻት ልጅ አላት፤ እከሌ እጮኛዋ አስረግዟት ሰሞኑን አስወረደች እያሉ በየመንደሩና በየቡና መጠጫው የሚያወሩ የምድር ጨው ሳይሆኑ የእንግሊዝ ጨው ናቸው:: የእንግሊዝ ጨው ሆድን አምሶ በሽታን የሚያስወግድ ሆኖ ሳለ፣ እነዚህ ግን በበሽታ ላይ በሽታ የሚጨምሩ

የወሬ ሱሰኞች ናቸው። እንደነዚህ ያሉት የምድር ጨው የዓለም ብርሃን ለመሆን የልብ ለውጥ ያስፈልጋቸዋልና ልንጸልይላቸው ይገባል።»

አዎ፣ ወገኖች፣ እኛስ ዛሬ በሕይወታችን የምድር ጨው ሆነን አልጫውን ዓለም፣ ቤታችንን፣ መንደራችንን፣ ቤተ ክርስቲያችንን፣ እያጣፈጥን ነው ወይስ እያመስንን? እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ ጨውና ብርሃን ሆነን በዓለም ኃጢአት ላይ ጨውን እንድንጨምር፣ በዓለም ጨለማ ላይ ብርሃንን እንድናበራ ጌታ ኢየሱስ ይርዳን። አሜን!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «የምድር ጨው ናችሁ. . . » (ማቴ. 5:13)።

ግጥምጥም:- ጨው አልጫ ሆኖ በምን ይጣፍጣል፣
ወደ ውጭ ተጥሎ በእግር ይረገጣል።

ዮሐ. 13:35
2ኛ ቆሮ. 6:14-15

# ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «አቤቱ፣... የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን» (መዝ. 19:14)::

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር የመነሻ አሳብን ይመዝናል:: <ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን> ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ውስጥን ይመለከታልና ግብዝነትን ከእኛ እናስወግድ:: ሰውን እንደምንሸነግል ወይም ሰውን እንደምናታልል እግዚአብሔርን ልናታልለው አንችልምና ግልጽነትን የተላበስንና የተደበቀ አጀንዳ ወይም ስውር ነገር የሌለን የእርሱ ልጆች ልንሆን ይገባናል:: እግዚአብሔር የውጭ ብቻ ሳይሆን የውስጥም አምላክ ነው፤ የአፍ ብቻ ሳይሆን የልብም አምላክ ነው:: ስለዚህ ፍቅራችን የልብ ይሁን እንጂ የአፍ ብቻ አይሁን:: ዛሬ ብዙ ሰዎች በቤታቸው እሾክና ጋሬጣ የሞላበት ሕይወት አላቸው:: በቤተ ክርስቲያን ግን ለስላሳ ናቸው:: ይህን አስመሳይነትህን ጌታ አንድ ቀን ሲገልጠው ትዋረዳለህና ተጠንቀቅ:: ይልቁንም የምትችለውን እችላለሁ፣ የማትችለውን አልችልም፤ የምታደርገውን አደርጋለሁ፣ የማታደርገውን አላደርግም ብለህ እውነትን በፍቅር ግለጽ እንጂ የማትችለውንና የማታደርገውን እፈጽማለሁ ብለህ <ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ> የሚሉትን የግብዞች ብሂል ፈጽሞ ከሕይወትህ አስወግድ::» ለሚለው ቀናና ግልጽ ለሆነ መልእክታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

ከደሃ ቤተሰብ ስለመጣች ሁልጊዜ ኑሮአቸው ከእጅ ወደ አፍ ብቻ እንደሆነ ታውቃለች:: ስለዚህም እንደ ጓደኞቿ የፈለገቻውን የልብስ ዓይነትና ጌጣጌጥ ማድረግ አትችልም:: ለዚህም ነው ሁልጊዜ በሁለቱም ጆሮዎቿ ላይ ደህና ቀን ሲመጣ ብርና ወርቁ ሲመጣ አደርግባቸዋለሁ፣ እስከዚያ ግን በሰበዝ ይቆዩ ብላ ሰበዝ የምታደርግባቸው:: ሰዎች ግን፣ «ሰበዝ በጆሮሽ ላይ የምታደርጊው ለምንድን ነው?» ብለው ሲጠይቋት፣ «ጌጤ ክርስቶስ ስለሆነ ሌላ ጌጥ አያስፈልገኝም» ብላ በውሸት ትመልስላቸው ነበር:: ታዲያ በዚህ መልሷ የተገረሙ ሰዎች፣ «በቀራኒዮ መስቀል ላይ የተሰቀለው ክርስቶስ እርሱ ጌጥሽ ከሆነ ታዲያ ለምንድን ነው ሰበዝ በጆሮዎችሽ ያደረግሽው:: ሰበዙንስ ለምን አትተይውም» ቢሏት፣ «አይ እንዳይደፈንብኝ ነው::» ብላ መለሰች::

አዎ፣ እግዚአብሔር የአፋችንን ሳይሆን የልባችንን ይመለከታልና በልባችን ያሰብነውን እንሁን:: በልባችን ጠልተን በአፋችን አንውደድ:: በልባችን ረግመን በአፋችን አንመርቅ:: በልባችን ተቃውመን በአፋችን አንስማማ::

ግጥምጥም:- ልብህ ያላለውን ተናግረህ የአፍህን፣
አፌ ቂቤ ሆነህ ልበ ጩቤ አትሁን::

> «አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ»
> (መዝ. 51:10)

# የአርባ ቀን ዕድሌ

መጋቢው፣ «እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር ሲያመጣን በከንቱ ሳይሆን በዓላማ ነው። የሠራንም ለሥራ ነው እንጂ ለመቀመጥ አይደለም። አምላክ በሰጠን ጸጋና ችሎታ ሁሉ፣ በሰጠን ዕድሜና ዘመን የበኩላችንን ድርሻ በታማኝነት ልንወጣ ይገባል። ስንፈጠር ድሃ ሆነን አልተፈጠርንም ወይም ለድህነት አልተመደብንም፤ ነገር ግን ሁላችንም የየራሳችንን ኃላፊነት (ሥራ) በታማኝነት ስለማንሠራና በሌላው ትከሻ ለመኖር ስለምንፈልግ ድህነት ወርሶናል። ስለዚህ ሁላችንም እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ እንደ እርሱ ፈቃድና ትእዛዝ ተግባራችንን ስንወጣ የሁላችንም ውጤት ተዳምሮ አገርን ይጠቅማል።» እያሉ ለተሰበሰበው ሕዝብ በሥራ የማደግ ባሕርይን ያስተምራሉ። ትምህርታቸውንም የበለጠ ለማስጨበጥ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«በአንድ አገር የሚኖር ንጉሥ ልደቱን ለማክበር ፈለገና እያንዳንዱ የአገሪቱ ኗሪ መሳተፍ አለበት ብሎ አስቦ ቀጣዩን አዋጅ አስነገረ። 'የአገሬ ሕዝብ ሆይ፣ ልደቴን በሚመጣው ወር መባቻ ላይ ስለማከብር ሁላችሁም ለግብር የሚሆን አንድ አንድ እንስራ ጠላ አዘጋጅታችሁ እንድታመጡ።' ይህንን አዋጅ የሰማ አንድ ሰው ጠላውን ማዘጋጀት ስንፍና ሆነበትና 'በጠላው ፋንታ አንድ እንስራ ውኃ ይዤ እሄዳለሁ' ብሎ አሰበ። 'ምክንያቱም ይህች የእኔ አንድ እንስራ ውኃ ከዚያ ሁሉ ጋን ጠላ ውስጥ ብትገባ ውኃነቷ ይጠፋል እንጅ አትታወቅም' ብሎ አሰበና በተቆረጠው የንጉሥ ልደት ማክበሪያ ቀን አንድ እንስራ ውኃውን ይዞ ሄደ። ሄዶም በጋኑ ውስጥ ሲገለብጥ በጋኑ ሙሉ ውኃ አዬ። ለካስ እርሱ ብቻ ሳይሆን አንድ እንስራ ውኃ ይዤ እሄዳለሁ ብሎ ያሰበው የአገሩ ሰው ሁሉ ነበርና የንጉሡ ልደት በውኃ ተከብሮ ዋለ።»

አዎ፣ ሁሉም በታማኝነት የራሱን ድርሻ ሲወጣ ተደምሮ መልካም ውጤት ያመጣልና ዛሬም በተሰማራንበት መስክ ሁሉ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳንል ሥራችንን እንሥራ፤ ዋጋችንንም እግዚአብሔር ይከፍለናል። በምድርም የዘራነውን መልካም ዘር እናጭዳለን። ድህነት የአርባ ቀን ዕድሌ ነው ብለን ደምድመን ተስፋ አንቁረጥ። የአርባ ቀን ዕድል የሚል ለድሃዎች የተሰጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። በውስጧ ለዓለም ሁሉ የሚበቃ ያልተነካ ሀብት በያዘች ድንግል መሬት ላይ ቁጭ ብለን ከማማረር እግዚአብሔር ይጠብቀን። አሜን።

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና» (ሮሜ 8:19)።*

ኤፌ. 2:10
2ኛ ተሰ. 3:6-10

ግጥምጥም:- *የአርባ ቀን ዕድሌ ብሎ ከማማረር፣*
*የአርባ ቀን ዕድልን ይሽላል መመርመር።*

# ደምህን አቁሜአለሁ

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «ነገር ግን ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ፤ ኃጢአተኝነታቸውን ከፊት ይልቅ ይጨምራሉና::» (2ኛ ጢሞ. 2:16)*

እንደተለመደው ከመኝታ በፊት በቁጥር በርከት ያለው ቤተሰብ በሙሉ ተገኝቶ አንድ ላይ የማታ የቤተሰብ ጸሎት አድርገን ነው የምንተኛው:: እና እስኪ ዛሬ አንድ ቃል ላካፍላችሁ ብለው ቁሉ ጀመሩ:: (የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ እየተገኙ የቤት ለቤት ፕሮግራሞች የመካፈሉ ጉዳይ በእጅጉ አሳስቧቸዋልና::)

«በትሕትናና በተሰበረ ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ለመንፈስ ቅዱስ ስንታዘዝ እግዚአብሔር ለሕይወታችን በቃሉ በኩል ይናገረናል:: ነገር ግን በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ይህንን ጉዳይ ሳናስተውል ከመቅረታችን የተነሣ ለእኛ ሌላ ሰው ቃል እንዲነግረን፣ ሌላ ሰው እንዲጸልይልን፣ ሌላ ሰው መገለጥ እንዲያመጣልን በመፈለግ ስንሯሯጥ እንገኛለን:: እነዚህ ነገሮች ሁሉ መልካም ቢሆኑም የእውነት መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚቀበሉ አገልጋዮች የመኖራቸውን ያህል በተቃራኒው ደግሞ የሐሰትን ቃል ከጥቅም ጋር አያይዘው የሚናገሩ፤ ሳይታያቸው ታየኝ፣ ተጨፍኖባቸው ሳለ ተገለጠልኝ የሚሉ መንፈሳዊ መሳይ አሳሳቾች አሉና ተጠንቀቁ:: መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ሁሉ ክርስቲያን፣ 'የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል' ያለ ሁሉ እውነተኛ ነቢይ አይደለም:: ይህን ሳስብ አንድ የሰማሁት አሳፋሪ ድርጊት ትዝ አለኝ፣ እርሱን ልንገራችሁ» ብለው የሚከተለውን ምሳሌ ፊታቸውን ከስክሰው እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

«አንድ ሰፈር ውስጥ የማታ የጸሎት ፕሮግራም አለ:: ይህንን ፕሮግራም ለመካፈል ሰው ሁሉ እየተጠራራ፣ 'አንድ መገለጥ ያለው ሰው አለ፣ ኑ እንሂድ' እያለ ይመጣል:: በዚያም ቀን ምንም እንኳን ጊዜው ክረምት ሆኖ ቢበርድም፣ ሁሉም ሰው ጋቢውን፣ ካቦርቱን፣ ብርድ ልብሱን እየለበሰ ታደመ፤ ፕሮግራሙም ተጀመረ:: ጥቂት ሰዓት ከተጸለየ በኋላ ያ ታዋቂ አገልጋይ የተባለው አንድ ብርድ ልብስ ተከናንቦ ወንድ ይሁን ሴት ምንነቱ በማይታወቅ የተንበረከከ ሰው ላይ እጁን ጭኖ እንዲህ ብሎ ተናገረለት፤ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ደምሽን አቁሜአለሁ ይላል' አለ:: ሰውዬው ደንግጦ 'ከንብንቡን አወረደና፣ 'ኧረ ወንድ ነኝ! ወንድ ነኝ!' አለ:: በዚህ ጊዜ ባለ ራዕይ ነኝ

ባዩ ሰው ማጣፊያው ቢያጥረው፣ 'አይ እንግዲህ ወንድም ብትሆን ደምህ ቆሞልሀል' ብሎት አረፈው::»

እዚህ ላይ ለአገልጋዮችም ለተገልጋዮችም መልዕክት አለኝ:: በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ ሲገለጥ ከክብር ይልቅ ውርደትን የሚያመጣ አገልግሎት አንስጥ፤ አንቀበልም:: የከበረውን የእግዚአብሔርን የጸጋ አገልግሎት በግል ጥቅም፣ ስምና ዝና እንዳንለውጠው እግዚአብሔር በቸርነቱ ያግዘን፤ የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍር ሠራተኛም ያድርገን:: አሜን::

*ግጥምጥም:- ያልተገለጠውን መግለጥ ከምትሞክር፣*
*የተገለጠውን ለመናገር ጨክን::*

ሕዝ. 34: 1-10

# ስኬት

ኮንፍራንሱን በጉጉት ሲጠብቅ ለነበረው ሕዝብ የዕለቱ ሰባኪ እንዲህ እያሉ መስበክ ቀጠሉ:: «በሕይወታችን ሁል ጊዜ መሳካት ሲገጥመን ሰይጣን ይህንን ተጠቅሞ እንዳይጥለን እንጠንቀቅ:: ብዙዎችን በመርዙ ወግቶ የጣለበት መሣሪያ አንዱ ስኬት ነውና ሁል ጊዜም በጠላት ወረዳ ውስጥ እንዳለን እናስብ እንጂ አንዘናጋ:: አሁን ያለንበትን ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከየት እንደመጣንም እናስብ፤ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ይከብራል፣ እኛም ከጠላት ፍላጻ እናመልጣለን:: መቼም ቢሆን ምቾት፣ ማግኘት፣ ክብር፣ ዝና፣ ተቀባይነት ሲመጣ የዚህ ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን አንርሳ:: እርሱን ከረሳንና ራሳችንን ከፍ ከፍ ማድረግ ከጀመርን ውድቀታችን ቀርቧል ማለት ነውና ተጠበቁ::» ለዚህ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ::

«በአንድ ወቅት በሁለት አገሮች መሐል ያለችውን ደሴት ለመያዝ ሁለቱም አገሮች ለጦርነት በባሕር ማዶና ማዶ ተሰለፉ:: የአንደኛው አገር የጦር ኃይሉ በጦሩ መሐል ቀዶ ሄዶ በጀልባ ቀድሞ ደሴቲቱ ላይ ባንዲራ እንዲተክልና እንዲይዛት ለአንዱ ጄኔራል ትእዛዝ ሰጠ:: ይህም ጄኔራል በጀልባው አንደኛ ጐን የእነርሱን አገር ባንዲራ፤ በሌላው ጐን የጠላታቸውን አገር ባንዲራ ሳለና በመሐላቸው ከተወሰኑ ወታደሮች ጋር ባንዲራዎቹን በሳለበት ጀልባ ላይ ሆነው ሲሄዱ፣ ወዲህ ማዶና ወዲያ ማዶ የሰፈረው የጦር ኃይል ሁሉም በራሱ በኩል የየአገሩን ባንዲራ ሲመለከት በደስታ አጨበጨበ፣ ጮኸ፣ ሁካታ አስተጋባ:: በዚህ አስደናቂ ሥራው ጄኔራሉ ተደሰተ፤ ስኬት በማግኘቱም ልቡ ተኩራራ:: የተላከበትን ዓላማ ባንዲራ ተክሎ መምጣት ሲገባው ሳይተክል ጭብጨባውና አክብሮቱ ጥሞታልና፣ 'አንድ ጊዜ ልድገመው እስኪ' ብሎ ዞሮ በመሐላቸው ሲመለስ ሁሉም አሁን የየራሱን ባንዲራ ሳይሆን የጠላትን ባንዲራ በመመልከቱ፣ ወዲህና ወዲያ ማዶ የሰፈረው ጦር ተኩስ ከፍቶ ሁለቱም ወገን በጥይት እሩምታ አርከፍክፈው ጄኔራሉን ከነወታደሮቹ ገደሏቸው::»

አዎ፣ ዝና፣ ክብርና ስኬት ጠላት ሰዎችን የሚጥልባቸው ዋና መንገዶቹ ናቸውና እንጠንቀቅ:: ጸልየን ሰዎች ቢድኑ፣ ሰብከን ሰዎች ቢጽናኑ፣ ትንቢትና መገለጥ አምጥተን ሰዎች ቢመለሱ፣ ስጦታውን፣ ችሎታውንና ጸጋውን ላበዛልን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን:: የራእያችን፣ የስኬታችን ምንጩ እግዚአብሔር ነውና፣ ጌታ ማስተዋሉን ያብዛልን::

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «... ባላጋራችን ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና...» (1ኛ ጴጥ. 5:8)::*

ዘዳግ. 8:11-18

*ግጥምጥም:- ዛሬ የሆንኩትን የሆንኩት በእርሱ ነው፣*

*ላከበረኝ ጌታ ክብሩን እሰጣለሁ::*

# መገለጥ ወይስ ማጋለጥ

ሰባኪው፣ «በዚህ ዘመን በአንዳንዶች ዘንድ ቅድሚያ እየተሰጠ ያለው ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለእኛ ክብር ሆኗል፤ እንዲታወቅ የሚፈለገው እግዚአብሔር ሳይሆን እኛ ራሳችንና ስማችን ሆኗል:: መቼም በየመንደሩና በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን የሚደረገው መንፈሳዊነት የመሰለው ግርግር አፍ አውጥቶ የሚናገረው ይህንን ነው:: ዛሬ ነቢይ ነን ባዮቹም ሆነ ነቢይ ፈላጊዎቹ የሚሯሯጡት ለራሳቸው ጥቅምና ክብር ሆኗል:: ይህንን ስናገር አዝናለሁ:: ሙሉ ሥልጣን ያለው ሕያው ቃሉ በቤታችን ሸልፍ ላይ አቧራ እየጠጣ ከቃሉ ውጪ የሆነ የምን ይታይሃልና ምን ይታይሻል በሰዎች ስሜትና ፍላጐት ላይ ያተኮረ የሥጋዊ መገለጥ ልምምድ እውነተኛ መገለጥ ሳይሆን ማጋለጥ ነው:: እውነትን የሚናገሩ እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒው ግን አንድም ነፍስ በማይድንበት ለጆሮአቸው የሚጥሙ የራሳቸውን አስተማሪዎች/ነቢያቶች/ እየጋበዙ /እየተጋበዙ/ በየመንደሩ በክርስቶስ ስም የሚደረገው መንፈሳዊ ግርግር ይቁም! የራስን ክብርና ዝና በመፈለግ እግዚአብሔር ያላሳየውን አየሁ፣ እግዚአብሔር ያልተገለጠውን ተገለጠልኝ እያሉ ወንጌልን ለሥጋ ድሎት ማኖሪያ ማድረግና የዋህ ሴቶችን እየሰበሰቡ ማደናገር ይቁም:: እግዚአብሔር ያላለውን፣ "ጌታ ፈውሶሃልና መድኃኒት እንዳትወስድ፣ ሐኪም ቤትም እንዳትሄድ" በማለት ሰዎችን መግደል ይቁም! "እግዚአብሔር ሊጠቀምብህ ይፈልጋልና ሥራህን ለቅቀህ ሙሉ ጊዜህን ካልሰጠህ ትቀሰፋለህ" በማለት ጌታ ባላለው መግባትና ቤተሰብን መበተን፣ ይልቁንም ጌታ ሳይፈውስ "ከኤች. አይ. ቪ. ኤይድስ ተፈውሰሃልና እከሊትን አግባ" ብሎ ሕዝብን መጨረስ ይቅር:: ለሚለው ጊዜያዊ ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ:-

አንድ መንደር ውስጥ ሁለት ሰዓት ጫማ ተወልቆ የሚገባበት ያለ አሥር ሰዓት የማይወጣበት መንፈሳዊ ፕሮግራም የሚካሄድበት የመሰለ ግን ከጥንቆላ ቤት ያልተናነሰ ሥራ የሚካሄድበት ቤት ነበር:: እዚያ ፕሮግራም ላይ እግዚአብሔር ያላለውን የሚል ዛሬ በዝና ፈረስ ላይ ወጥቶ ሽምጥ የሚጋልብ ነገ ግን ተከስክሶ ከነመታሰቢያው ሊጠፋ የተዘጋጀ ነቢይ ነኝ ባይ ሰው እንዲህ ብሎ ተናገረ:: «በዚህ እንዳትኖሪ ተለዩ ይልሻል ጌታ» ብሎ ተናገረ:: ይህ መልእክት ለእኔ ነው ብላ የተቀበለች ሴት ከዚያ ጊዜ ጀምራ ሦስት ከወለደችለት ባለቤቷ ተለይታ

ልጆቿን ይዛ ወጥታ ዛሬ ከነልጆቿ የምትበላው አጥታ በረሐብ አለንጋ እየተቀጣች ትገኛለች።

አዎ፣ ወገኖቼ ሆይ፣ እግዚአብሔር ያጣመረውን ከመለየት እንቆጠብ። እኛን የሚያኖረን ምላሳችን ሳይሆን እግዚአብሔር ነው፤ ብልጠታችንና ጥበባችን ሳይሆን በእግዚአብሔር መታመናችን ነው። ስለዚህ ያላየነውን ከመናገር ያየነውን ተናግረን እንሙት። ያልተገለጠልንን ተገለጠልን ከማለት የተገለጠውን ወንጌል ብቻ እንስበክ፣ እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ነውና።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑን ጨለማ ለሚያደርጉ፤ ጣፋጩን መራራ መራራውን ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው።»

ግጥምጥም:- «ሳይታየኝ ታየኝ ብሎ ከማጨለም፣

ሁሌም በሕይወቱ አምላክ ያየው ይቅደም።

| |
|---|
| ኢሳ. 5:20-21 |
| 2ኛ ጢሞ. 3:6-7 |